2023

# የሐዋርያው ጳውሎስ የድነት መልዕክቶች

## ገላቲ ያ እና ሮ ሜ

*ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። ገላ2፡16*

TCM

**በክርስቲያናዊ አስተምህሮ አገልግሎት**

# መግቢያ

ሐዋርያው ጳውሎስ በአገልግሎቱ ለብዙዎች ወንጌልን ሰብኮአል እጅግ በጣም ብዙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ተክሎአል ፣ ቅዱሳንን አጽናንቶአል አበረታቶአል እንዲሁም ወደ 13 ወይም 14 የሚደርሱ ደብዳቤዎችን ጽፎአል። ሁሉም መልዕክቶቹ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆኑ ሥነ-መለኮታዊ ትምህርቶችን የያዙ ቢሆኑም እነዚህ የድነት ደብዳቤዎቹ ግን እጅግ ጥልቅ የሆኑ ሐሳቦችን ያቀረበበት ነው።

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናል ብሎ አስቦ ተዘጋጅቶ ባይጽፋቸውም በእግዚአብሔር መንፈስ እየተነዳ በመጻፉ ምክንያት መለኮታዊ የሆነ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ገላጭ መልዕክቶች ሆነዋል። በመሆኑም እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገውን የሰዎችን ልጆች የማዳን ሥራ ትልቅ አፅንዖት ተጥቶታል። በተለይም ደግሞ አይሁድም ሆኑ አሕዛቦች በአንድ አካል በክርስቶስ ያለ ልዩነት የተስፋውን ቃል ወራሾች መሆን በጳውሎስ ሥነ-መለኮት ውስጥ ትልቅ ትንታኔ የተሰጠበት ነው። በተጨማሪም አይሁድ ከእግዚአብሔር የማዳን አጀንዳ አንጻር ያላቸው ስፍራ ከየትኛውም የጳውሎስ መልዕክቶች ይልቅ ትልቅ ሽፋን የሰጠበት መልዕክቱ ነው።

እነዚህን ሁለት መጽሐፎች በአንድነት ለማጥናት አስፈላጊ የሆነበት ዋናው ምክንያት የሁለቱም መጽሐፎች መልዕክት ተመሳሳይነት ነው። በተለይም ጽድቅ በሥራ ሳይሆን በእምነት የሚገኝ ብቻ መሆኑን በተለያየ ገጽ ሊያሳዩ የቻሉ በመሆናቸው ነው። ሥለዚህም በእርጋታ እና በጥሞና በጸሎት ሆኖ ማጥናቱ ለመንፈሳዊ ሕይወት እና አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ትልቅ ትኩረት እንድትሰጡት በጌታ ፍቅር ላሳስብ እውዳለሁ።

የጌታ ሰላም እና ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን !

## ማውጫ

ገጽ

### ክፍል ፩

### የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ገላቲያ ሰዎች


1. የገላቲያ መጽሐፍ መግቢያ ........ 3
2. ስለ እውነተኛው ወንጌል የቀረበ መከላከያ 1-2 ........ 10
3. ስለ እውነተኛው ወንጌል ምንነት የቀረበ ገለጻ 3-4 ........ 15
4. በእውነተኛው የወንጌል ሥርዓት መመላለስ 5-6 ........ 19


### ክፍል ፪

### የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


5. የሮሜ መጽሐፍ መግቢያ ........ 22
6. ለሰዉ ሁሉ አዳኝ ማስፈለጉ 1፡17-3፡20 ........ 26
7. እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያዘጋጀው አዳኝ 3፡21-5፡21 ........ 30
8. በወንጌል የመጣ የነጻነት መንገድ 6-7 ........ 32
9. በመንፈስ ቅዱስ የተገኘ አርነት 8 ........ 33
10. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አጀንዳ ለእስራኤላዊያን 9-11 ........ 34
11. በእውነተኛው የወንጌል ሥርዓት መመላለስ 12፡1-15፡7 ........ 37
12. ሰላምታ እና የማጠቃለያ ሐሳብ 15፡8-16፡27 ........ 38

# ክፍል ፩
# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ገላቲያ ሰዎች

## 1. የገላቲያ መጽሐፍ መግቢያ

አንድን መጽሐፍ ልናጠና ስንነሳ ልንከተለው የሚገባው መንገድ የመጽሐፉን መሰረታዊ እውነታ መፈለጊያ ጥያቄዎችን በመጠቀም ነው። በመሆኑም የገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት መልዕክት የሆነውን ይህንን የሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤን በአግባቡ ለመረዳት በእነዚህ ጥያቄዎች መሰረት ይሆናል።

### *ሀ. የመጽሐፉጸሐፊማንነው ?*

- በመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ እንደ ተገለጠው ከሌሎች የሐዋርያው መልዕክቶች ይልቅ ግልጽ ፣ለየት እና ጠንከር ባለ አገላለጥ እራሱን የገለጠበት ክፍል በመሆኑም እራሱ ጳውሎስ ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።
- እርሱ ስለ ጻፈው መልዕክት ከማውሳታችን በፊት ግን ስለ ጸሐፊው በቂ ግንዛቤን ማግኙቱ መልዕክቱን በተገቢው መንገድ ለመረዳት ስለ ሚጠቅም መጠነኛ ሐሳቦችን እናነሳለን።
- ጳውሎስ ማን ነው?
    - በኬልቂያ ክፍለ ሀገር በጠርሴስ ከተማ አይሁድ ከሆኑ ቤተሰቦች ተወልዶ ያደገ ሰው ነው። ለዚህም ነው የሮማዊ ዜግነትን ያገኘው። የሐዋ22፡3
    - ከጠርሴስ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ በአይሁድ ሥርዓት እና እውቀት እንዲያደግ በወላጆቹ በወቅቱ በአይሁድ ሥነ-መለኮት እጅግ ታዋቂ በመሆነው በገማልያ እግር ሥር ተቀምጦ ስለ ሕግ፣ ስለ አይሁዳዊነት ወግና ሥርዓት ጠንቅቆ የተማረ ነው።
    - ከዚህ ትምህርቱም የተነሳ ለሃይማኖቱ እጅግ ቀናተኛና ፈሪሳዊም ሲሆን፤ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ እና የሰማዕታቱ የእስጢፋኖስ ሞት ሁሉ ተባባሪ ነበር። ከዚህም ባለፈ ከወቅቱ የአይሁድ ሽማግሌዎች እና ሊቀ ካህናት የፈቃድ ደብዳቤን በማውጣት ከኢየሩሳሌም ከተማ በስደቱ ምክንያት የወጡትንና የተበተኑትን አማኞች ሁሉ ለማሳደድ እስከ መሰማራት የደረሰ ነው። ይህንንም ተግባር ለመፈጸም በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በታላቅ ብርሃን ተገልጦለት ወደ እውነተኛው ወንጌል ፊቱን የመለሰ ሰው ነው። የሐዋ 9፡1-10፤ 22፡6-11

- በደማስቆ በሐናንያ እጅ መጫን ነሰሐ ገብቶ እና ከተጸለየለት በኋላ በውሃ ተጠምቆ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከአይኑም እንደ ቅርፊት የሚመስል ነገር ወደቀለት። ወዲያም ያሳድደው የነበረውን መንገድ በደማስቆ በድፍረት መስበክን ጀመረ። ይሁን እንጂ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ ደቀመዛሙርትም ይህንን ተረድተው በቅርጫት አድርገው በአጥር ላይ አወረዱት ከሞትም አምልጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደ። የሐዋ9፡10-25፤22፡12-16
- በኢየሩሳሌም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሊቀላቀልና ሊተባበራቸው ቢሞክርም እውነቱን ስላልመሰላቸው እና መለወጡን በመጠራጠራቸው ሳቢያ ቶሎ ሊቀበሉት አልቻሉም። በተወደደው ወንድም በበርናባስ ምስክርነት ሳቢያ ሁሉም አምነው ተቀበሉት በጸጋም ብዙ ይጠቅማቸው ጀመር ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለአይሁድ አጥብቆ ይመሰክር እና ይሰብክ ነበር። ይሁን እንጂ በሁለት ምክንያቶች በኢየሩሳሌም ለመቆየት አልቻለም ፡-
    1. አይሁድ በቅናት ሊገድሉት ስለ ወደዱ
    2. ጌታ በደማስቆ መንገድ ለወንጌል አገልግሎት ወደ ሩቅ ድረስ እንደሚሔድ በተናገረው መለኮታዊ ጥሪ ሳቢያ ነው፤ የሐዋ 9፡26-30፤22፡17-21
- ከዚህ በኋላ ጳውሎስ በደማስቆ ፣ በአረብ እንዲሁም በኪልቂያ አገሮች ተንቀሳቅሶአል። በእርግጥ እነዚህን ወቅቶች እና ጊዜያቶች አስማምቶ ማስቀመጥ ግን እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ እስከ አሁን ድርስ ቆይቶአል። ሆኖም ግን ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ ለወንጌል ጥሪው ሹመት እና ለጌታ ጸጋ አልፎ መሰጠት ምክንያት የሆነችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናዋ ከመምጣቱ በፊት በርናባስ ከኪልቂያ ለአገልግሎቱ እንዲረዳው አስበ እንዳመጣው ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል። የሐዋ9፡30፤11፡25-26 ፤ 22፡21 ፤ ገላ1፡17
- ጳውሎስም ሳውል በሚል መጠሪያው ስሙ በሶሪያ አንፆኪያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከነቢያት እና ከመምህራን ጋር በፆም በጸሎት በማስተማር እና በአምልኮ በአንድነት ሲተጉ ለታላቁ የወንጌል ተልዕኮ መነሻ የሚሆን ድምጽ መጥቶ ተጸልዮላቸው ሳዉል እና በርናባር ወጡ። የሐዋ 11፡19-26፤ 13፡1-4

ከዚህ በኋላ እጅግ ታላላቅ የወንጌል መሠረት የተጣለባቸው እና የጳውሎስ መለኮታዊ ጥሪ ለአሕዛብ ሐዋርያ መሆኑን ያረጋገጡ ሥራዎች የተሠሩበት ጊዜ ሲሆን የወንጌል ጉዞዎች እጅግ ሰፊ እና ረጃጅሞችም ነበሩ።

1. የመጀሪያው የወንጌል ጉዞ ፡- በዚህ ጉዞ ወቅት የነበሩት በርናባስና ሳዉል ሲሆኑ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ደግሞ አገልጋያቸው ሆኖ ጉዞአቸውን ወደ ሴሌውቅያ፣ ወደ ቆጵሮስ፣ወደ ስልማና ፣ወደ ጳፉ ፣ ወደ ጴርጌን ፣ ወደጵንፍልያዋ አንፆኪያ ፣ወደ ኢቆንዮ ፣ወደ ልስጥራን እና ወደ ደርቤን ከዚያም ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ መጡ። በዚህ ጉዞአቸው ነበር የደቡብ ገላቲያ አውርጃ አብያተ ክርስቲያናት የተተከሉት።
2. ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ ፡- ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ የጳውሎስን አዲስ የወንጌል አሰራርን ጨምሮ ተነሳ፤ ይኸውም አስቀድሞ የተተከሉትን በቅደሚያ በመጎብኘት ከዚያ ወደ አዲስ አቅጣጫን መሔድ የሚል ነበር። በጉዞውም ዝግጅት ወቅት በርናባስ እና ጳውሎስ እስኪከፋፋ ድረስ በማርቆስ አብሮ መሔድ እና አለመሔድ ዙሪያ ጭቅጭቅ ሆነ። በመሆኑም በርናባስ ማርቆስን መረጠ ሳዉል ግን ሲላስን መረጠ የደቡብ አብያተ ክርስቲያናት ለመጎብኘት በየብስ ጉዞ በማድረግ ተጀመረ። በመሆኑም በልስጥራን ወጣቱን ጢሞቲዎስ አግኝቶ ወደ ቡድኑ ተጨመረ ቀጥሎም በጢሮአዳ ሉቃስ ወደ ቡድኑ ተጨመረ። በዚህ ጉዞ ወቅት የደቡብ ገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንዳሉ ሲጎበኙ አዲስ የወንጌል እርሻዎች ደግሞ ፊልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ ፣ ቤርያ ፣ አቴና ፣ ቆሮንቶስ እና ኤፌሶን ነበሩ። የሐዋ 15፡41፤ 16፡1-3፤10 ፤ 15፡41-18፡22
3. ሶስተኛው የወንጌል ጉዞ ፡- በዚህ ወቅት የወንጌል ስርጭቱ ቡድን በጣም ብዙ ሰዎችን ያካተተ መሆኑ ይታወቃል። በእርግጥ ከዚህ ጉዞ መሐል ነበር የሮሜ መልዕክት ለቅድመ ዝግጅቱ እንዲጠቅም በማሰብ የተጻፈው። ምክንያቱም የጳውሎስ የወንጌል ቀጣይ ትኩረት እስፔን ነበር። በዚህ ጉዞ ወቅት  አስቀድሞ የተተከሉትን መጎብኘት በገላቲያ በኩል ወደ ኤፌሶን ፣ መቄዶንያ ፣ጢሮአዳ፣ ሚሊጢን፣ ጢሮስ እና ቂሳሪያ ነበሩ። በኤፌሶን ለሶስት ዓመት ተቀምጦ ጢራኖስ በሚባል ትምህት ቤት ውስጥ ያስተምር ነበር ይሁን እንጂ ተቃውሞ በመነሳቱ ወደ መቄዶንያና አካያ አገር መጣ።

በየከተማው የአይሁድ ሴራ እየበረታ በመሔዱ እና ለበዓልም ጭምር ወደ ኢየሩሳሌም መጣ በዚያም እስራት ጠበቀው።

4. አራተኛው የወንጌል ጉዞ፡- ይህ ጉዞ በእርግጥ ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ የተጓዘበት ቢሆንም ቅሉ ወንጌልን ለመስበክ ሰፊ በር የተከፈተለት ጊዜ ነበር
    - ወደ ሮሜ ከመጓዙ በፊት በቂሳሪያ ለሁለት ዓመት ቆይቶ ነበር በዚህ ወቅትም ነበር በአግሪጳና በፊልክስ ፊት ቀርቦ ስለ ጌታ የመሰከረው። የሐዋ23፡33-26፡32
    - ይህም የመጀመሪያው እስር ጊዜው ነበር የሐዋርያት ሥራም መጽሐፍ ይህንን ዘገባ በመተረክ ነው የሚያበቃው። በዚህ ወቅት ነበር የእስር ቤት ደብዳቤዎች የተጻፉት። ከዚህ እስራት ወጥቶም ጳውሎስአጥቢያዎችን በማደራጀት በማስተማር እና ወንጌልን በመስበክ እንዳሳለፈ ከመልዕክቶቹ መረዳት ይቻላል።

- ሐዋርያው ጳውሎስ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ መንገድ ለሁለተኛ ጊዜ እስር ቤት ይገባል በዚያም ሳለ የመጨረሻ መልዕክቱን 2ኛ ጢሞቴዎስ እንደ ጻፈ ይታሰባል የሕይወቱ ፍጻሜም በ68 ዓ.ም ነው ተብሎ ይገመታል።
- ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በብዙዎች ዘንዳ መስማማት ባይኖርም ለግንዛቤ ያህል መጥቀሙ አይቀርምና በሰንጠረዥ ተቀምጦአል።

## ሰንጠረዥ 1

| የሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት እና የወንጌል አገልግሎት ጊዜ የሚያሳይ ሰሌዳ | | |
|---|---|---|
| ክንውኖች | ዓመተ ምህረት | የጳውሎስ የወንጌል ጉዞዎች እና መልዕክቶች |
| የጳውሎስ መለወጥ | 31/32 | |
| ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱ | 37 | |
| ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱ (በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የተዋጣ ብር ይዞ) የሐዋ11 | 45 | |
| | 45-49 | • የመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ |
| | 49 | • የገላቲያ ደብዳቤ |
| ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱ<br><br>ለስብሰባ የሐዋ15 | 49/50 | |
| | 50-53 | • ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ |
| | 52/53 | • መልዕክቶች - 1 እና 1 ተሰሎንቄ |
| ለአራተኛ ጊዜ ወ ደኢየሩሳሌም መምጣቱ | 53 | |
| | 54-58 | • የሶስተኛው የወንጌል ጉዞ |
| | 57 | • 1ኛእና 1ኛቆሮንቶስ |
| | 57 | • ሮሜ |
| በኢየሩሳሌም የታሰረበት | 58 | |
| በቂሳርያ የታሰረበት | 58-60 | |
| የመጀመሪያው የሮም እስር | 60-63 | |
| | 62 | ቆላስይስ፣ኤፌሶን፣ፊልሞና |
| | 63 | ፊልጵስዩስ |
| ከእስር የተለቀቀበት | 63-67 | - ተጨማሪ የወንጌል ጉዞዎች |
| | 67 | - 1ኛጢሞቲዎስ እና ቲቶ |
| ሁለተኛው የጳውሎስ እስር በሮሜ | 68 | - 2ኛጢሞቴዎስ |
| የጳውሎ ስመሰዋት | 68 | |

## *ለ. የመልዕክቱ ተቀባዮች እነማን ናቸው?*

- በመልዕክቱ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጠው ለገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ስለሚል አጠራጣሪ ሊሆን አይችልም። አስቀድመን እንደ ተመለከትነው በሐዋርያው የመጀመሪያ የወንጌል ጉዞ ወቅት ለተመሰረቱት ለደቡብ የገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ነው።
- በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የዳኑት አማኞች በትውልዳቸው አሕዛብ የነበሩ እና ጌታ ለወንጌል ልባቸውን የከፈተላቸው ሕዝቦች ናቸው። በመሆኑም ምንም ዓይነት የእውነተኛው አምላክ ግንኙነትም ሆነ እውቀት ከዚህ በፊት ያልነበራቸው እና ከዚህ ቀደም ስላላቸው የአምልኮ ሕይወታቸው ከግምት በቀር የተገለጠ ነገር የለም።

## *ሐ. መልዕክቱ የተጻፈበት ዋና ምክንያት*

- በመሠረቱ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድ የዳኑ ቅዱሳንን የያዘች ሆና ነው የጀመረችው ምክንያቱም ወንጌሉ ለአይሁዳዊያን ብቻ ነበር የሚሰበከው በመሆኑም የአይሁዳዊነት ተጽዖዕኖ በጣም ከፍተኛ ነበር ፤ ነገር ግን ከትንሽ ቆይታ በኋላ ለወንጌሉ ከአሕዛብ ወገን ምላሽ መስጠት በመጀመራቸውና ምላሻቸውም ፈጣን እና ሰፊ በመሆኑ ፤ በአሕዛብ ዘንድ የደረሰው ወንጌል ከሚገመተው በላይ አድጎ አብያተ ክርስቲያናት እየተተከሉ ሔዱ አይሁድ እና አሕዛብ በአንድነት ሆነው ክርስቶስን ለማመለክ እጅግ ተቸግረው ነበር። ይህንንም ተከትሎ ከፈሪሳዊያን ወገን የዳኑት የሕጉን አስፈላጊነት ለአሕዛብም መሰበክ አለበት ብለው መነሳታቸው በመካከላቸው ያለውን ውጥረት ጨምሮት ነበር።
- በሥነ መለኮት መምህራን ዘንድ ይህ ጊዜ የሽግግር ጊዜ ነው ብለው ይላሉ ማለትም ከሕግ ወደ ጸጋ። በተለይም ደግሞ ለዚህ እንደ ምልክት የሚጠቀሱት
    - ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ወርዶ ወንጌሉን ከአይሁድ ውጪ ለሆነ ሕዝብ መስበኩ የመጀመሪያው እርምጃ ተደርጎ ሲወሰድ - የሐዋ8፡1-25
    - የጳውሎስ መለወጥ እና ለአሕዛብ የሚሆነውን ወንጌል ይዞ እንዲነሣ መጠራቱ የሽግግሩ አካል ሁለተኛው ደረጃ ተደርጎ ይወሰዳል - የሐዋ9፡1-19

- ○ የጴጥሮስ አገልግሎት በቂሳሪያ የሽሽግር ጊዜው ሶስተኛ እርምጃ ተደርጎ ይወሰዳል በዚህም ወቅት ቆርኔሌዎስ እና ቤተሰቡ በሙሉ ዳኑ የመንፈስ ቅዱስንም የስጦታ ተቀበሉ በውሃም ተጠመቁ፤
- ○ የሶርያዋ አንጾኪያ በሚገርም ሁኔታ በአህዛብ የተሞላች ትልቅ ቤተ ክርስቲያና መሆን የሽሽግግሩ አካል አራተኛ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል የሐዋ11፡19-26
- ○ በየሩሳሌም የተጠራው ጉባዔም የአሕዛብን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መፍለስ ማሠሪያ የሰጠ እና ማጠቃለያ ነበር። በመሆኑም ስብሰባው አይዳዊነትን ከክርስትናው ለይቶ አስቀመጠ። ይሁን እንጂ የችግሩ አሳሳቢነት ወደ መፍትሔ እንደመራቸው ግን ማየቱ ተገቢ ነው።

- በርናባስ እና ሳዉል የገላቲያን አውራጃዎች ለቀው ከሔዱ በኋላ የአይሁድ ወግ እና ሕግ አጥባቂዎች በየቦታው እየዞሩ የክርስቶስን ወንጌል በማመን በጸጋ ብቻ መዳን በቂ አይደለም መገረዝ እና ሕግን መጠበቅ ተገቢ እና ተገቢ ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር። ይኼንኑ ትምህርታቸው በገላቲያ አውረጃዎች አስተምረው በቶሎ ተቀባይነት አግኝተው ነበር። ለዚህ ደግሞ የረዳቸው የሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል የመስበክ ሥልጣን ጥያቄ ውስጥ በማስገባት ትክክለኛ መብት የሌላው እና ለዚህም ሙሉ ሥልጣን የሌለው ሰው ነው በማለታቸው በቶሎ እንዲሰሙ እና ከሰሙትም እውነተኛ ወንጌል ወደ ኋላ እንዲመለሱ ሆኑ።
- ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን በማወቁ በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ የወለዳቸውን አጥቢያዎች ወደኋላ እንዳይመለሱ ለማረም እና ጥያቄ ውስጥ የገባውን የሐዋርያነቱን ሥልጣን ለመከላከል መነሻ ያደረገ መልዕክት ነው።

## *መ. የመልዕክቱ ዋና/ አብይ ሐሳብ*

- የገላትያ መልዕክት ሰው የሚድነው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደ ሆነ አጉልቶ የሚያሳይ መልዕክት ነው። ክርስቶስ ከሕግ እስራት እና ከኃጢያት ባርነት ነፃ አውጥቶናል በመሆኑም እንደገና በባርነት ቀበር አትያዙ ይልቁን ጸንታችሁ ቁሚ የሚል አብይ ሀሳብን የሚየሳይ ነው። 2፡16፤5፡1

### *ሠ. መቼት*

- የገላቲያ መልዕክት የተጻፈው ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ጉባዔ ከመሔዱ አስቀድሞ ነው። ምክንያቱም በኢየሩሳሌም የነበረው ጉባዔ "አሕዛብ ሕጉን መታዘዝ ያለባቸው እስከ ምንድር ድረስ ነው?" የሚለው አጀንዳ ለመወያየት ሲሆን ጉባዔውም በውሳኔው ያጸደቀው *"...ነገር ግን ከጣዖት ርኵሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቈርጣለሁ"* የሐዋ15፡20። በማለት ብቻ ነበር ስለሆነም ይህንን ሐሳብ በደብዳቤው ሊያካትተው ይችል ነበር። ስለዚህ የተጻፈበት ጊዜ ከዚህ ቀድም ባለው ጊዜ በ49 ዓ.ም ሊሆን ይችላል።
- የተፃፈውም የወንጌል ጉዞ መነሻ ከሆነቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያ ነው።

### *ረ. የመልዕክቱ ይዘት*

- የገላቲያን መልዕክት በሶስት ክፍል ይዘቱን ማጠቃለል ይቻላል
  - ጳውሎስ እውነተኛው ወንጌል እንዳይበረዝ ለመጠበቅ ያቀረበው መከላከያ ሐሳቦች የያዘው ክፍል ከምዕ1-2 ያካተተው ሲሆን ፤
  - ጳውሎስ ለሰው ልጆች ሁሉ መዳን ትክክለኛ መንገድ የሆነውን የክርስቶስን ወንጌል ምንነት የገለጸበት እና ያብራራበትን ክፍል የያዘው ከምዕ3-4 ያካተተው ነው፤
  - ጳውሎስ የእውነተኛውን ወንጌል የኑሮ ሥርዓት ለመኖር እንዴት እንደሚቻል ከምዕ5-6 ያብራራበት ነው።

## 2. ስለ እውነተኛው ወንጌል የቀረበ መከላከያ 1-2

- ሐዋርያው ጳውሎስ ከአይሁድ የሕግ አክራሪዎች የተነሳውን ተግዳሮት እውነተኛው ወንጌል ከመበረዝ ለመጠበቅ የመከላከያውን ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት የሙሉ ደብዳቤው አጠቃላይ መግቢያ የሥነ-ጽሑፍ ሥርዓትን የተከተለ አቀራረብ አለው። ይህም አቀራረቡ በሁሉም መልዕክቶቹ ላይ የተለመደም ነው።

✧ *1፡1-5 የመልዕክቱ መንደርደሪያ፤*

ሀ. የመልዕክቱ ባለቤት መሆኑን እራሱን የገለጠበት -

- ከጳውሎስ
    - በኢየሱስ ክርስቶስ
    - እርሱንም ከሙታን ባነሳው በእግዚአብሔር አብ - ሐዋርያ የሆነው፤ ( ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ) ይህ አገላለጡ ከሌሎቹ የደብዳቤዎች የሚለይ ነው። "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሐዋርያ የሆነ.." የሚለው የተለመደው የጳውሎስ አገላለጥ ሲሆን ለዚህ እንደ ምክንያት ሊቀርብ የሚችል የሐዋርያነቱን ስልጣን ጥያቄ ውስጥ ያስገባውን ሐሳብ ለመቃወም ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የሐዋርያነቱ የሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር ወልድ እና አብ ናቸው እንጂ በሰው በኩል ወይም በቀጥታ ከሰው ያልተገኘ ነው በማለት በሰላምታ ክፍል ውስጥ የውስጡን ስሜት የሚገለጥ ይመስላል።
- ከእርሱም ጋር ካሉት ወንድሞች - ምናልባትም በርናባስ እና ሌሎች በወቅቱ በአንጾኪያ የነበሩ አገልጋዮችን የሚጠቅስ ነው።

ለ. የመልዕክቱ ተቀባዮች - ወደ ገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸው ተጠቅሶአል።

ሐ. ሰላምታ - በሐዋርያው መልዕክቶች ሁሉ ላይ ጸጋ እና ሰላም የተለመደ የሐዋርያው የሰላምታ አገላለጥ ነው። ለጢሞቴዎስ እና ለቲቶ በጻፈው መልዕክቱ ላይ ብቻ "ጸጋ ምሕረት እና ሰላምም" በሚል አገላለጽ ለየት ከሚለው ውጪ ሁሉም አንድ ናቸው።

መ. የድነታችን መሰረቱ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ እና በእግዚአብሔር ወልድ እራስን አሳልፎ መስጥ ላይ መስረት ያደረገ በመሆኑ ለአብ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን በሚል ሐሳብ የመንደርደሪያው ክፍል ይጠናቀቃል።

✧ *1፡6-10 - ከእውነተኛው ወንጌል የተለየ የሚሰብክ ሁሉ እርጉም ነው፤*

- በገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በመጀመሪያው የወንጌሉ ጉዞ ወቅት በክርስቶስ ጸጋ ወደ እግዚአብሔር የጠራቸውን እውነተኛውን ወንጌል ትተው ፈጥነው ወደ ልዩ ወንጌል አልፈዋል።
- ይህንን ልዩ ወንጌል የሰበኩት
    - <u>የሚያናውጡ</u> አናዋጮች
    - ወንጌሉን <u>የሚያጣምሙ</u> አጣማሚዎች

- ሾልከው <u>በስውር የገቡ ሐሰተኛ</u> ወንድሞች (2፡4) ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰዎች ማንነት መሰረቱ አይሁዳዊያን እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም የሚሰብኩት ሐሳብ የአይሁድን ሥርዓት ፣ ወግ ፣ መገረዝን እና ሕግን ጭምር ነው፡፡ የክርስቶስ ወንጌል በውል ያልገባቸው ፣ በእርግጥ ዳግም እንደ ተወለዱ እርግጠኛ መሆን በማይቻል ሁኔታ ውስጥ ሆነው በዳኑት አይሁድ መካከል ያሉ አሳሳቶች ናቸው፡፡

- የሐዋርያው ጳውሎስ ማሰሪያ ግን ለእነዚህ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ይህንን ወንጌል ሊለወጥ ሊቀይር ለሚነሳ ሁሉ ነው፡፡ ጳውሎስ እኛም ብንሆን መላዕክትም ቢሆኑ ሌሎች ሰዎችም ቢሆኑ ከተሰበከው ወንጌል የተለየ የሚሰብኩ ሁሉ የተረገመ ይሁን ብሎ በከፍተኛ ኃይለ ቃል ይናገራል፡፡

### ✧ *1፡11-24 በጳውሎስ የተሰበከው ወንጌል ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠለት ነው፤*

- ወደ ገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ገብተው ልዩ ወንጌል የሰበኩ የሕግ አክራሪዎች በቶሎ ተቀባይነት እንዲያገኙ እና የዳኑት ቅዱሳን ወደ መናወጥ የከተታቸው መሰረታዊ ጉዳይ የወንጌል ሰባኪው ሐዋርያው ጳወሎስ የአገልግሎቱ የሥልጣኑ ምንጭ ትክክል አይደለም በሚል የሐሰት ሐሳብ ነው፡፡
- ከ12ቱ ደቀመዛሙርት ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ ያልተመረጠ እና አብሮ ያልነበር ሲሆን በኢየሩሳሌም ካሉት የጌታ ሐዋርያት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው በመሆኑ የወንጌል ሰባኪነቱን ኃላፊነትም ሆኑ መልዕክቱ አጠያያቂ ነው የሚል ሰበብ ሣያቀርቡ አይቀርም፡፡
- የሐዋርያውም መልስ
  - በእኔ የተሰበከ ወንጌል ከሰው አልተቀበልኩትም ደግሞም አልተማርኩም ፤
  - አስቀድሞ በአይሁድ ስርዓት በከፍተኛ ቅናት እና ነቀፋ የምኖር ሰው ነበርኩ ፤
  - ከዚህም የተነሳ ቤተ ክርስቲያንን አሳድድ እና አጠፋ ነበር ፤
  - ነገር ግን ገና ከእናቴ ማህፀን ሳለሁ ነው ጌታ በጸጋው ለዚህ አገልግሎት የጠራኝ ፤
  - እኔም ፈቃዴን በፈቃዴ ሰጥቼ ወደ ሌሎች ሐዋርያትም ሆኑ ዋና ወደ ሆኑ እንኳን አልሔድኩም ስለዚህም የምስበከውን ወንጌል ከማንም አልተማርኩም አልሰማሁም በመሆኑም የሰበኩላችሁ እና የሰማችሁት ወንጌል ፍጹም እውነት እና ታማኝነትን የተለባሰ ነው፡፡

### ✧ 2፡1-10 በጳውሎስ የተሰበከ ወንጌል ማንም ምንም ያልጨመረበት ነው፤

- የሕግ አክራሪዎች በገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ልብ ውስጥ ስለ ጳውሎስ ሐዋርያዊ የስብከት አገልግሎት ላይ ያጣሉት ጥላ የሰሙትን እውነት እንዲጠራጠሩ አድርጎአቸዋል፤ በመሆኑም በእርሱ የተሰበከው የእውነት ወንጌል ከሐዋርያት ዋና መስለው በሚታዩ እና በሚታወቁ እንኳን ምንም እርማት እንዲሁም ጭማሪ ያልተደረገበት ስለ መሆኑ ማስረጃ ያቀርባል።

  1. ወደ ኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ የሔደበት መሰረታዊ ምክንያት - እግዚአብሔር ገልጦልኝ ነው የሔድኩት እንጂ ሰው አዞኝ አይደለም የሚል ስሜት ያለው ነው። መሠረታዊ ጉዳዩም የቤተ ክርስቲያን መሪ ለነበሩት ሰዎች የምሰብከውን ወንጌል ለማሳየት እንጂ የምሰበከውን እንዲሰጡኝ አልነበረም የሚል ሙግታዊ ሀሳብ ያቀረበበት ክፍል ነው።

  2. ጳውሎስ ለሚሰበከው የወንጌል እውነት ትክክለኛነት በኢየሩሳሌም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ የነበረውን ስሜት እንደ አንድ ማስረጃ አድርጎ አቅርቦአል

     - አብሮ ከሔዱት መካከል የግሪክ ተወላጅ የነበረው ቲቶን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲገረዝ አላስገደዱትም ፤

     - ያዕቆብ ዮሐንስ እና ጴጥሮስ ለአይሁድ ወንጌልን ለማድረስ እንደ ተጠሩ ፤ጳውሎስ እና በርናባስ ደግሞ ለአሕዛብ የሚሆነውን ወንጌል ለማድረስ እንደ ተጠራ አወቁ። በመሆኑም በአገልግሎቱ ለድሆች ትልቅ ትኩረት እንዲሰጥ ለመኑት፤

     - እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ የማያደላ በመሆኑ ለኬፋ ሐዋርያ እንዲሆን የሰራለት ለእኔም ሐዋርያ እንድሆን ሰርቶልኛል በማለት በአገልግሎቱ የእግዚአብሔር አብሮነት እንደ አንድ ምስክርነት አቅርቦአል።

### ✧ 2፡11-21 - ሐዋርያው ጴጥሮስ በጳውሎስ መገሰጹ፤

- ሐዋርያው ጳውሎስ በአክራሪ አይሁድ በገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ሐዋርያነቱ ምንም ባለመሆኑ ሳቢያ የሚሰብከውም ወንጌል ትክከለኛነቱ አጠራጠሪ እንደሆነ አድርገው ቢያቀርቡትም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን እውነተኛውን ወንጌል ለመከላከል ያቀረበው ሙግት ጴጥሮስ በአንጾክያ

መጥቶ በግብዝነት ሕይወት ሲመላለስ ሌሎች የዳኑ አይሁድ በርናባስም ጭምር በግብዝነቱ ተስቦ ስለ ነበር ፤ ይህ ሁኔታ ቅንነት ያለበት ኑሮ ባለመሆኑ እና ለተገለጠው ወንጌል ተቃራኒ በመሆኑ የወንጌልን እውነት ለማስተካከል ጳውሎስ የወሰደው እርምጃ ነበር፤

1. ጴጥሮስን ፊት ለፊት ገሰጸው፤ፍርድ ይገባው ነበርና ፤ ምክንያቱም
   - ጴጥሮስ እግዚአብሔር ወንጌሉን ለአሕዛብ ጭምር እንደሆነ አስቀድሞ መገለጥን አግኝቶአል። በመሆኑም የቆርኔሌዎስ ቤተሰብ በሙሉ በእጁ ድነዋል።
   - መዳን በክርስቶስ ጸጋ ብቻ እንጂ በሕግ ሥራ እንደማይዳን ጴጥሮስ ያውቃል ይሰብካልም፤ በመሆኑም ከኢየሩሳሌም አንዳንድ ወንድሞች ከመምጣታቸው በፊት ከአሕዛብ ጋር ይበላ እና ይጠጣ ነበር። በሰዓታት ልዩነት ነው የተለወጠው ይህ ደግሞ ከአንድ መሪ በውቅቱ በፍጹም የማይጠበቅ ጉዳይ ነው። እየገነባ የነበረውን ጉዳይ ጴጥሮስ መልሶ በአካሔዱ እያፈረሰው ነው።
2. የጴጥሮስ አካሔድ ክርስቶስን የኃጢያት አገልጋይ የሚያደርግ እና እግዚአብሔር በነፃ የሰጠንን የክርስቶስን ጸጋ የሚያስጥል ነው። በመሆኑም የጳውሎስ ሙግት ለጴጥሮስ
   - ጽድቅ በክርስቶስ በማመን ብቻ በመሆኑ አይሁዳዊያን ሆነን በክርስቶስ ወንጌል አምነናል፤
   - የሕግን ሥራ በመጠበቅ መዳን እንደማይቻል አውቀናል፤
   - ክርስቶስን ይዘን ሕግን ለመጠበቅ ምንነሳ ከሆነ ክርስቶስ አላስፈላጊ ነው ደግሞም የኃጢያት አበረታች ወይም አገልጋይ ነው፤
   - ሕግ በመጠበቅ ጽድቅን ለማምጣት የምንጥር ከሆነ የእግዘአብሔር ነጻ ስጦታ አለመቀበል በመሆኑ የእግዚአብሔርን ጸጋ ጥለናል በማለት አስገራሚ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ገለጻ ያለበት ግሳጼ እንደሆነ እንረዳለን። ይህ ሁኔታ ለገላቲያ አብያተ ክርስቲያናት ስነ-ልቦናዊ ጥቃት ትልቅ መልስ ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣን የሌለው እና የሚሰብከውም ወንጌል ዋና ከሚመስሉ ሐዋርያት ጋር የማይገናኝ አድርገው ላቀረቡላቸው ሐሳብ ተገቢ መልስ በመሆኑ ነው።
   - የጳውሎስ የማጠቃለያ ሐሰቡ በዚህ ጥቅስ ነበር እስቲ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት

*"እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና።ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።" ገላ2፡19-20*

## 3. ስለ እውነተኛው ወንጌል ምንነት የቀረበ ገለጻ 3-4

- በዚህ ክፍል ውስጥ በዋናነት የእውነተኛው ወንጌል ምንነት እና ያመጣው በረከት የተገለጠበት ነው።

✧ *የእውነተኛው ወንጌል ምንነት ከገላቲያ አማኞች ሕይወት አንጻር 3፡1-5*

- የገላቲያ አብያተ ክርስቲያን አማኞች በነበራቸው ሕይወት ውስጥ ካሳለፉት ነገሮች በማንሳት ጳውሎስ ወደ አምስት የሚሆኑ መልስ የማያስፈልጋቸው በውስጣቸው ግን የመልሳቸው ምንነት ግልጽ የሆኑ ሐሳቦች ያነሳባቸዋል።

1. "..የገላትያ ሰዎች ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?"
   - እውነት ማለት ለሰዎች ሁሉ ድነት ቤዛ ለመሆን በመስቀል ላይ የሞተው ኢየሱስ በመሆኑ ይህንን የእግዚአብሔር የቤዛነት ሥራ ተሰብኮላቸው ነበር ለዚህ ትልቅ እውነት እንዳይገዙ ያፈዘዛችሁ ጉዳይ ነው የሚጠይቃቸው።
2. "...በሕግ ሥራ ወይስ ከእምነት ጋር በመሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁ?"
   - የቀድሞ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እና ጥምቀት ልምምዳቸውን በማንሳት ይህንን መለኮታዊ ሥጦታ የተቀበላችሁት የተሰበከላችሁን ወንጌል ስምታችሁ በእምነት በመቀበላችሁ ያገኛችሁት ወይንስ ሕግን በመጠበቃችሁ ምክንያት ያገኛችሁት መልሱ ይታወቃል በገላትያኑ ዘንድ።
3. "እንዲህ የማታስተውሉ ናችሁ?በመንፈስ ጀመራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁ?"
   - ይህ ሰስተኛው ጥያቄ ከሁለተኛው ጥያቄ ጋር የተያያዘው ነው። የክርስትና ሕይወታቸው የተጀመረው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነበር ምክንያቱም ያለ መንፈስ ቅዱስ የሆነ የሚሆንም ነገር የለምና። እሁን ግን ሕግን በመጠበቅ

እግዚአብሔርን ለማስደሰት መነሳት ጀምረዋል ይህ ደግሞ አለማስተዋል ነው። በዚህ ምዕራፍ ለሁለተኛ ጊዜ ነው"...የማታስተውሉ.." የሚለው ቃል የተጠቀሰው ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የገላቲያ አማኞች ነገሮችን በጥልቀት ለመመልከት አለመቻላቸውን አመላካች ነው።

4. "በውኑ ከንቱ እንደ ሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን?"
   - የገላቲያን አማኞች ወንጌል በተቀበሉ ጊዜ ብዙ ስደትን እና መከራን ተቀብለዋል። ይህም ስድት እና መከራ ስለ ክርስቶስ መስቀል ምክንያት የደረሰባቸው ነው። ዛሬ ግን ያንን ሁሉ ዋጋ ከከፈሉ በኋላ ለመመለስ መነሳታቸው ከንቱነት የሞላው የሕይወት ጉዞ መሆኑን ለማሳየት ነው።
5. "እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ፥ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?"
   - ይህም ጥያቄ ወንጌል አስቀድሞ በእነርሱ ዘንድ በተሰበከ ጊዜ ልዩ ልዩ ተአምራቶች ተደርገው ነበር። እነዚህ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች የተከናወኑት ሕግን በመጠበቅ የመጡ ወይስ እውነተኛው ወንጌል ሰምቶ በማመን?በእርግጥ መልሱ በልባቸው ውስጥ አለ።

- በእነዚህ አምስት ጥያቄዎች ጳውሎስ የገላትያ አማኞች በልባቸው ትክክለኛውን መንገድ ማየት እና ማስተዋል የቻሉ ዘንድ ለማስቻል ነው። በመሆኑም ከሕግ ሥራ የተለየው ወንጌል የክርስቶስ መስቀል ሞት ላይ የተመሰረተ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ፍጻሜን የሚያገኝ ፣ በመከራ የታጀበ እና በተአምራት የሚጸና ነው።

### ✧ *የእውነተኛው ወንጌል ምንነት ከቅዱሳን መጻሕፍት አንጻር ሲብራራ 3፡6-14*

- ጳውሎስ በገላትያ አማኞች ዘንድ የተፈጠረውን በሰው ችሎታ ላይ የተመሰረተውን የሕግ ስራ በተመለከተ ከክርስቶስ ወንጌል አንጻር ከቀደሙት ቅዱሰት መጻሕፍት በማጣቀስ ያብራራል። እነዚህ የብለይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ እውነተኛው ወንጌል ያላቸውን ትርጉም ማሳየት እጅግ ተገቢ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሕግ አጥባቂ አይሁዳዊያን እነዚሁን መጻሕፍት ነው ለግል ሐሳባቸው እንዲመች አድርገው በማጣመም ያስተማሯቸው።

- ቁ. 6 - ዘፍ 15፡6 "አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።" - የአብርሃም እምነት ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረት በመሆኑም አብርሃም በስራ ሳይሆን ጻድቅ ሆኖ የታየው በአምላኩ ፊት በእምነት ነው። ስለዚህም በእምነት ወደ እግዚአብሔር ቀርበው ጽድቅ የሚወስዱ ሁሉ የአብርሃም ልጆች ናቸው።
- ቁ 10 - ዘፍ27፡26 "የዚህን ሕግ ቃሎች ያደርግ ዘንድ የማያጸና ርጉም ይሁን፤ ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይላሉ።" ፡- በሕግ ሥራ ጸንቶ የማይተገብረው ሁሉ ሕጉ ራሱ ርጉም ይሁን ብሎ ረግሞታል። ሰው ከደካማ ባሕርይው የተነሳ ሕግን ሁሉ ፈጽሞ መጠበቅ አይችልም። ምክንያቱም አትግደል የሚለውን ጠብቆ ነገር ግን ቢያመነዝር ሕግን ሁሉ አፍርሶአል። ያዕ2፡10-11 በመሆኑም ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሕግን ሥራ በመጠበቅ ጻድቅ ሊሆን አይችልም ።
- ቁ. 11 - ዕንባ2፡4 "...ጻድቅ ግን በእምነቱ በሕይወት ይኖራል።"፡- ማንም በሕይወት ሊኖር ቢወድ በእምነቱ እንጂ በሕግ ሥራ አለመሆኑን ለማስረገጥ የተጠቀበት ምንባብ ነው። ጳውሎስ ይህንን ጥቅስ በገላ3፡11 ፣ በሮሜ1፡17 እንዲሁም ዕብ 10፡38 በተደጋጋሚ ስለሚጠቀም የእርሱ ጥቅስ ተደርጎ እስኪወሰድ ደረስ ሆኖአል።
- ቁ 12 - ዘሌዋ18፡5 "የሚሠራቸው ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖራልና ሥርዓቴንና ፍርዴን ጠብቁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"፡- በዚህ ቃል መሰረት ሕግ መታዘዝን እንጂ እምነትን አይጠይቅምስለዚህም በሕግ በኩል በሕይወት የሚኖረው ሰው በፍጹም ለሕጉ መታዘዝ የሚችል ነው። ይህን ደግሞ ማድረግ የሚችል ማንም ሰው የለም።
- ቁ. 13 - "በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጠህን ምድር እንዳታረክስ በእርግጥ በዚያው ቀን ቅበረው።" ፡- ክርስቶስ ከሕግ በታች ኖሮእንዲሁም በሕጉ መሠረት እርጉማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን። ስለዚህ በክርስቶስ የመስቀል ሞት ምክንያት ሁላችንም ከሕግ እርግማን ነጻ ወጥተናል።

- በጥቅሉ ሐዋርያው ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ሊያሳይ የፈለገው እና የምንመለከተው ዋና እና አብይ ሐሳብ "ሰው የክርስቶስን ወንጌል ሰምቶ በማመን ብቻ ጻድቅ ይሆናል። ይህም ጽድቅ ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብ ሁሉ መሆኑን በግልጽ ለማሳየት ችሎአል።

### ✧ የእውነተኛው ወንጌል ምንነት በተስፋ ቃል ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ 3፡15-18

- ለአብርሃም የተነገረው ተስፋ "በአንተ በዘርህ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ" የሚለው የተስፋ ቃል ፍጻሜ የሚያገኘው በክርስቶስ ነው። ይህም የተሰፋ ቃል ደግሞ አይሁድን እና አሕዛብን አይለይም። በመሆኑም አይሁድም ሆኑ አሕዛብ እንደ ተስፋው ቃል በክርስቶስ ይባረካሉ። ይህ ደግሞ ሕግ ከመሰጠቱ ከ430 ዓመት በፊት የተነገረ ነው። ምንም እንኳን ሕጉ ከተስፋው ቃል በኋላ ቢመጣም የተስፋውን ቃል ግን አልወጠውም አልሻረውምም።እንዲሁም እሰራኤላዊያን ከግብጽ ወጥተው የከነዓንን ምድር የወረሱት በተስፋው ቃል ላይ ባላቸው በእምነት እንጂ በሕግ አማካይተን አይደለም።

### ✧ የሕጉ ምንነት 3፡19-25

- ከላይ በተዘረዘሩት ሐሳቦች ውስጥ ጳውሎስ ስለ ተስፋው ቃል እና በሕግ መዳን ሰለ አለመቻል እያብራራ መጥቶአል። በመሆኑም የሕግ ትርጉም እና አስፈላጊነት የት ድረስ እንደሆነ ማብራራት ደግሞ ተገቢ ነው። ምክንያቱ አላስፈላጊነቱ ከድነት አንጻር ከተነገረ ሥራው ደግሞ ምን እንደነበር መገለጽ አለበት።
- ሕግ
    - ✧ አስቀድሞ የተነገረው የተስፋው ቃል ክርስቶስ እስኪመጠ ድረስ በመላዕክት በኩል በሙሴ አማካኝት ኃጢያት ምን እንደሆነ እንዲታወቅ ተሰጠ፤
    - ✧ እምነት እስኪመጣ ድረስ ጠባቂያችን ነበር፤
    - ✧ የተስፋ ቃል ወደ ሆነው ክርስቶስ የሚያደርሰን ሞግዚታችን ነበር፤
    - ✧ አሁን ግን የተሰፋው ቃል ክርስቶስ በመምጣቱ ከእንግዲህ ወዲህ ሞግዚታችን አይደለም።

### ✧ በእውነተኛው ወንጌል የተገኘ መንፈሳዊ በረከት 3፡26-4፡7

- በሕጉ ያልሆነ ነገር ግን ደግሞ በእምነት ከሆነው ከክርስቶስ ወንጌል የተገኘው ፍጹም በረከት ጳውሎስ ለገላቲያ ሰዎች እንደገና ለማሳየት ይሞክራል። እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶች
    - በእምነት በኩል ሁላችንም በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጀነትን አግኝተናል፤
    - የክርስቶስን ሞት እና ትንሳዔ ለመተባበር የተጠመቅን ሁላችን ክርስቶስን ለብሰነዋል፤

- በክርስቶስ ወንጌል ያመንን ሁላችን አንድ ነን እንጂ በዘር ፣ በጎሳ እና በሥራ የሚመጣ ልዩነት መካከላችን የለም። በመሆኑም እግዚአብሔር ለአይሁድ እና ለሕዛብ የተለየ ልብ የለውም።
- አይሁድ የሚመኩበት አብርሃም በእምነት በክርስቶስ የሁላችን አባት ሆኖአል።
- በእምነት ለአብርሃም የተገባውን ተስፋ ሁሉ የወራሽነት መብት አግኝተናል።
- ከሕግ በታች ተጠብቀን ሳለ የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ከሴት የተወለደውን ልጁን ልኮ ልጆቹ እንድንሆን ከሕግ የበላይነት እግዚአብሔር ዋጅቶናል።
- የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት በክርስቶስ ስላገኘን እግዚአብሔር አባታችን አባ አባ ብለን መጮህ የምንችልበትን የልጅነት መንፈስን ሰጥቶናል።
- በመሆኑም ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር ልጆች እንጂ ባሪያዎች አይደለንም።

✧ *በእውነተኛው ወንጌል የተገኘው መታዘዝ መሸርሸሩ 4:8-20*

- በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ከገላቲያ አብያተ ክርስቲያን ዘንድ በመጀመሪያው የወንጌል ስርጭት ጊዜ የነበረባቸውን የእርስ በእርስ ግንኙነት በማንሳት እንዴት ወደኋላ ለመመለስ እንዳሰቡ እና ወደኋላ የሚስቧቸው ለበጎ እንዳልሆነ በማሳሰብ ፤ ክርስቶስን እንደገና በውስጣቸው ለመሳል ምጥ እንደያዘው እንዲሁም ከእነርሱም የመጀመሪያውን የመታዘዝ መንፈስ እንደገና እንደሚሻው ያስገነዝባቸዋል።

✧ *እውነተኛው ወንጌል በምሳሌ ሲብራራ 4:21-31*

- ከሕግ በታች ለመኖር የሚወዱ ሰዎች ሁሉ ሊረዱት የሚገባውን እውነት ጳውሎስ የሣራ ደንገጡር በመሆነችው በአጋር እና ከአብርሃም ሚስ ከሣራ በተወለዱት ልጆች ምሳሌ የተስፋው ቃል የወለዳቸውን እና በሕግ ጥላ ስር የሚኖሩትን በማሳየት ያስረዳል።

## 4. በእውነተኛው የወንጌል ሥርዓት መመላለስ 5-6

- ሐዋርያው ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች እስከ አሁን ሲከላከል እና ሲያስረዳ የነበረውን ሐሳብ ወደ ማጠቃለል እመጣ ነው። በመሆኑም ከመንፈስ ቅድስ በሆነ እምነት ሰው የጸድቃል እንጂ በሕግ ሥራ ማንም እንደማይጸድቅ በብዙ መንገድ እና ጎዳና ሲያስረዳ ነበር።

- እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ግን ሁለት ነጥቦችን የሚያመለክት ሐሳቦች ይዘዋል የመጀመሪያው ሐሳብ በሕግ መጽድቅ እንደማይቻል ያቀረበውን ሙግት ማጠቃለያ የሰጠበት እና በዕለታዊ ኑሮ እንዴት መኖር ወይም መመላለስ እንዳለበቻው የሚናገርበት ነው።

### ✧ *የጳውሎስ ሙግት ማጠቃለያ 5፡1-12*

- ክርስቶስ በሞቱ እና በትንሣዔው ከሕግ እስራት ነጻ አውጥቶአችዋል በመሆኑም እንደገና ተመልሳችሁ በሕግ እስራት ውስጥ ለመግባት አትፈልጉ።
- ሰው ቢገረዝም እንኳን ምንም አይጠቅመውም ምክንያቱም መገረዝ እንዳለ መገረዝ አለመገረዝም እንደ መገረዝ በመሆኑ ነው። በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝም አለመገረዝም ምንም ትርጉም የለውም።
- ሕግን በመጠበቅ በእግዚአብሔር ፊት ለመጽደቅ ሰው የሚፈልግ ከሆነ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ነፃ ስጦታውን ማለትም ጸጋውን ጥሎአል።
- እኔ ጳውሎስ መገረዝን ሰብኬ ቢሆን ኖሮ ምንም ዓይነት መከራ ባልተቀበለኩ ነበር በመሆኑም የጸጋውን ወንጌል በመስበኩ ብዙ ስደት መከራ እና ድብዳባ ደርሶበት ስለነበር በሥጋዬ ላይ ይህንን ድብዳባ የሚያሳዩ ሰንበሮች ወይም ጠባሳዎች አሉኝ ይህ ለእኔ ትምክቴ ነው እንጂ መዋረጃዬ ባለመሆኑ ከዚህ ትምክቴ በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ በማለት የደረሰበትን መከራ ለበጎ እንደሆነ በማሳሰብ ትገረዙ ዘንድ የሚያስገድዳችሁ መገረዝ አይደለም መቆረጥ ይችላሉ በሚል ኃይለኛ ቃል ያስረዋል።
- እነዚህ ሕግ አክራሪዎች
    - እራሳቸው እንኳን ሕግን ጠባቂዎች አይደሉም፤
    - ትምክተኞች ናቸው ፤
    - በሰው ሁሉ ፊት መልካም መስለው ሊታዩ የሚወዱ ናቸው።
    - መገረዝን የሚሰብኩት በክርስቶስ መስቀል ምክንያት መከራና ስደት እንዳይደርስባቸው ብቻ ነው።
- ይህ አይነቱ የሕግ አክራሪዎች ማባበል ከጠሪያችን ከእግዚአብሔር የወጣ ወይ የመጣ ባለመሆኑ ልናስብብት ይገባል።

### ✧ *የዕለት ተዕለት ክርስቲያናዊ ኑሮ 5፡13-6፡18*

- የፍቅር ሕግ ይገዛናል ምክንያቱም የሕግ ሁሉ ማሰሪያ ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የምትል በመሆንዋ ነው። ስለዚህም አንዳችን ለአንዳችን በፍቅር በመተሳሰብ መኖር ይጠበቅብናል። እርስ በእርሳችን መነካከስ ወይም መጠላለት ግን በክርስቶስ የተሰጠንን በሕግ ጥላ ስር የማድር እስራት ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይመራን መጠንቀቅ አለብን የሚለው የመጀመሪያው የጳውሎስ ማሳሰቢያ ነው።
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና ፈቃድ መመላለስ የክርስቶስ ወንጌል ትሩፋት ነው። በመሆኑም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመላሱት ለሥጋዊ ምኞት ተግባር የተጋለጡ አይደሉም። ስለዚህም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት የሚከለክላቸው ነገር አይኖርም።
- በመንፈሳዊ ነገር ዳካማ የሆኑ ማቅናት እና የሌሎችን ሸክም በመሸከም የክርስቶስን ሕግ መፈጸም የሚጠበቀው የአዲሱ ኑሮ ሥርዓት ነው።
- ቃሉን በማስተማር ሌሎችን የሚያገለግሉ እና የሚደክሙ ከሚገለገሉት ሥጋዊ ነገር ደግሞ የማግኘቱ ጉዳይ በጎ እና መልካም ነገርን እንደ መከፋፈል ይቆጠራል። ደግሞም በመዝራት እና በማጨድ ሕግጋት ውስጥ ማለፍ ግዴታ ነው። ምክንያቱም የዘራነውን ያኑን ነገር ማጨዳችን አይቀርም።
- ጽድቅ በክርስቶስ ወንጌል አምኖ የሚገኝ እንጂ በሕግ ሥራ ጽድቅን ማግኘት አይቻልም በዚህ ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ሰላም እና ጸጋ ይበዛል። በማለት ጳውሎስ የገላትያ መልዕቱን ያጠናቅቃል።

# ክፍል ፪

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## 5. የሮሜ መጽሐፍ መግቢያ

- የሮሜ ሰዎችን መልዕክት ለመረዳት አንድን መጽሐፍ ለማጥናት የምንከተለውን እውነታ መፈለጊያ ጥያቄዎችን በማንሳት እንጀምራለን። ይህንን ማድረጋችን የሚጠቅመን ስለ መልዕክቱ የታሪክ ጀርባ እና የጸሐፊውን የልብ ፍላጎ ምን እንደ ነበር በመረዳት በመልዕክቱ ላይ ትክክለኛ ፍቺ ለማግኘት ስለ ሚረዳን ነው።
- በመሆኑም የመልዕክቱን መግቢያ በሁለት ክፍል ከፍለን እንመለከታለን።
    - የመጀመሪያው የመጽሐፉን መሠረታዊ ሐሳብ ወይም መልዕክት ለመረዳት በሚያስችሉን እውነታ መፈለጊያ ጥያዎች መሰረት ሲሆን፤
    - ሁለተኛው ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፈው መልዕክቱ ላይ በተለይ ከቁጥር 1-16 ባሰፈረው የደብዳቤው መንደርደሪያ መግቢያ ሐሳብ መሰረት ይሆናል።

### *5.1 መሠረታዊ እውነታ መፈለጊያ ጥያቄዎች*

### *ሀ. የጸሐፊው ማንነት*

- የዚህ መልዕክት ባለቤት በመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ በመገለፁ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ ማንነት፣የአገልግሎት ሕይወት እና ፍጻሜ በገላቲያ መጽሐፍ ጥናት መግቢያ ላይ በሰፊው ተመልክተናል።
- ከሐዋርያው ጳውሎስ አፍ እየተቀበለ በፊደል ያስቀመጠው ፀሐፊ ግን ጤርጥዮስ ነው። 16:22

### *ለ. የመልዕክቱ ተቀባዮች*

- የዚህ ደብዳቤ ተቀባዮች በወቅቱ ዓለምን ሁሉ ይገዛ እና ያስተዳድር በነበረው የሮም መንግስት ዋና ከተማ በሆነችው በሮሜ የሚኖሩ አማኝ ክርስቲያኖች ናቸው። በነቢዩ ዳንኤል ትንቢት መስረት ዓለምን እንዲመሩ እግዚአብሔር አሳልፎ ከሰጣቸው ከሰው መንግስታት መካከል ሮም የመጨረሻዋ ናት።

ጌታችን በተወለደበት፣ አገልግሎቱን በመጀመረበት ፣ በሞተበት እና በተሰነሳበት ጊዜ የእስራኤልን ምድር ሁሉ ትገዛ እና ታስተዳድር የነበረች ናት። እንዲሁም ሐዋርያት ለታላቁ ተልዕኮ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ዓለምን በሚያናውጡበት ጊዜም የዓለም ሁሉ ገዢ እና አስተዳደሪዋ ይህቺው አገር ናት።

- ይህች ታላቅ ግዛት ያላት መንግስት ግዛቷን ለማስፋፋት እና ለመቆጣጠር ይረዳት ዘንድ ዓለምን በቀላሉ ሊያገናኙ የሚችሉ ታላላቅ መንገዶችን ሰርታላች በመሆኑም " መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ያመራሉ" የሚሉ አባባሎች እስኪነሩ ድረስ ሆኖአል በተጨማሪም ጎዳናዎች ከወንበዴ የጸዱ እንዲሆኑ የተደረገበት ጊዜ ስለነበር የሮም ዜግነት ለሌለው ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር እጅግ ያስቸግር ነበር።
- በንግዱ ዘርፍ ታላላቅ የግሪክ መረከቦችን ጨምሮ በባሕር ላይ ጉዞ ማድረግ በውቅቱ እጅግ የተለመደ ነበር።
- በፓለቲካው ፣ በኢኮኖሚው በወታደራዊ ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ከዓለም ሁሉ ዙሪያ ባለ ጉዳዮች በከተማዋ ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ የተለያዩ መልክ እና ገጽታ ያላቸው ሕዝቦችን የምታስተናገድ ከተማ ናት ሮም።
- በእርግጥ በሮም የምትገኘው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በማን እና እንዴት እንደተመሰረተች የሚታወቅ ነገር የለም ይሁን እንጂ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ ለበዓለ ሃምሳ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት አስራ ምስት አገሮች መካከል አንዷ ሮም ናት። ምናልባትም እነዚህ ለበዓል መጥተው በጴጥሮስ ስብከት አምነው በተጠመቁ አማኝ ክርስቲያኖች ልትመሰረት ችላለች ተብሎ ይገመታል።
- በአጥቢያዋ ውስጥ በሰፊው አሕዛብ እና መጠነኛ አይሁድ በአንድነት ሆነው እንደሚያመልኩ ከደብዳቤው አጠቃላይ ገጽታ መመልከት ግን ይቻላል። ይህን ሁኔታ የፈጠረው ምናልባትም ከተማዋ የውቅቱ የሮም መንግስት መናገሻ በመሆንዋ ሊሆን ይችላል።
- ጳውሎስ ስለሮሜ አማኞች መንፈሳዊ ሕይወት ግንዛቤ ያለው ይመስላል ምክንያቱም በመካከላቸው ያለውን መጠነኛ ችግሮች ለማረም ፣ለማስተካከል ብሎም መንፈሳዊ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ የሚረዳ መልዕክት ነው የጻፈላቸው። በሌላ አቅጣጫም በሰላምታውም ላይ የሰዎችን ስም እየጠቀሰ ነው ሰላምታ ያቀረበው ይህም ትውውቅ እንዳላቸው የሚያስረዳ ነው። 15፡14-16፤ 16፡1-16

### ሐ. መልዕክቱ የተጻፈበት ዋና ምክንያት

- ጳውሎስ በጻፈው መልዕክቱ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጣው በአውሮፓ የጀመረውን የወንጌል ተልዕኮ ወደ እስፔን ይዞ ለማለፍ ያሰበበት ጊዜ ነው። በመሆኑም ወደ እስፔን ለማለፍ በጉዞው እንዲረዱት በማሰብ አስቀድመው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁት ለማድረግ የጻፈው መልዕክት ነው።
- በተጨማሪም ወደ እስፔን በሚያደርገው ጉዞ ወቅት እግረ መንገዱ አጥቢያዋን መጎብኘትንም አስቦአል። የሮሜን ቤተ ክርስቲያን ለመጎብኘት ብዙ ጊዜ ቢያስብም ወደ እዚያ እንዳይሔድ በመከልከሉ ሳቢያ ሊያያቸው እና ሊያገለግላቸው አልቻለም። አሁንም በድጋሚ እግረ መንገዱን ሊያያቸው አቅዶአል። ስለዚህም በእኔ እና በእናንተ ማካከል ባለች እምነት አብረን እንድንጽናና ጸጋንም እንድንከፋፈል ተዘጋጅቻለሁ በክርስቶስ የበረከት ሙላት እንድመጣ አሰባለሁ በማለት ሊያገልላቸው እንዳሰበ ለመግለጥ እና እነርሱንም ለማሰናደት የተላከ መልዕክት ነው። 1፡9-15፤ 15፡23-24

## መ. የመልዕክቱ ዋና ሐሳብ

- አሕዛብ ሕግ ባይኖራቸው ከኃጢያት በታች ናቸው ፤ ሕግ ያላቸው አይሁድም ቢሆኑ በሕግ ሥራ ጽድቅን ሊያገኙ አልቻሉም ሁሉም ከኃጢያት በታች በመሆናቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል። በመሆኑም እግዚአብሔር ከእምነት ብቻ የሚገኝ የራሱን ጽድቅ አዘጋጅቶአል ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በማመን እውን ሆኖአል የሚለው የሮሜ መልዕክት እምብርት ነው።
- በተጨማሪ ግን አይሁድ ከዘላለሙ እግዚአብሔር የማዳን እቅድ አንጻር ያላቸውን ስፍራ ከምዕ 9-11 ባለው ክፍል ውስጥ ሰፊ ሽፋን አግኝቶአል።

## ሠ. የመልዕክቱ መቻት

- የሐዋርያው ጳውሎስ ሶስተኛው የወንጌል ጉዞ ማጠናቀቂያ አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም ለመምጣት በዝግጅት ላይ እያለ በ57 ዓ.ም ሳይጽፈው አልቀረም።
- በዚህ ወቅት በቆሮንቶስ ከተማ አሊያም ደግሞ በክንከራያስ ሊሆን ይችላል።

### ረ. የመልዕክቱ ልዩ ባሕርይ

- የሮሜ መልዕክት ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ በክርስቶስ እምነት ብቻ ስለሚገኘው የእግዚአብሐየር ጽድቅ የሚያስረዳ ብቸኛ መጽሐፍ ነው።

- በተለይም ደግሞ እስራኤልን አስመልክቶ
    1. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አጀንዳ የሆነው የሰው ልጆች መዳን ከእስራኤላዊያን አንጻር እንዴት እንደሚታይ ሊያስረዳ አቅም ያለው ብቸኛው መልዕክት ነው።
    2. የጳውሎስ የግል ስሜቱ በሥጋ ዘመዶቹ ስለ ሆኑት እስራኤልያዊያን ከክርስቶስ ወንጌል አንጻር የተገለጠበት ነው። እራሱን እስኪረግም ድረስ ስለ እስራኤላዊያን መዳን ያለው ቅናቱ እና ምኞቱ ግልጽ የሆነበት መልዕክት ነው።

## *5.2 የሐዋርያው ጳውሎስ የመልዕክቱ መንደርደሪያ ሐሳብ 1:1-16*

- ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እጅግ ሰፊ እና ጥልቅ የሰው ልጆች የድነት መንገድን ገላጭ መልዕክቱን ከመጀመሩ በፊት እንደ ተቀሩት መልዕክቶቹ ሁሉ ደንብን የተከተለ የደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓትን ይዞ ቀርቦአል፤
    - *እራሱን ያስተዋውቃል* - ጳውሎስ እራሱን የሚጠራበት እና ለሌሎችም እራሱን የሚያስተዋውቅበት መንገድ
        - ሐዋርያ (መልዕክተኛ) ለመሆን በእግዚአብሔር የተጠራ፤ ይህ የሐዋርያነት ሹመት ብቻ ሳይሆን ሰዎች በተለይም አሕዛብ ከአፉ በሚሰሙት መልዕክት በእምነት እንዲታዘዙ የሚያስችል ጸጋ (መለኮታዊ ብቃት) ጭምር የያዘ በመሆኑ "ጸጋንና ሐዋርያነትን" ተቀበልን ይላል።
        - የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ፤
        - አስቀድሞ በነቢያት ለተነገረው ተስፋ የተለየ በማለት ይገልጻል።
    - ከሮሜ ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት - የመልዕክቱ ተቀባዮች የሆኑ የሮሜ አማኞች በጳውሎስ ገለፃ መሰረት ፤-
        - የተጠሩ ናቸው - የኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆን እና ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩ መሆናቸውን ገልፆ በእግዚአብሔር የተወደዱ ናቸው ይላል።
        - በክርስቶስ ኢየሱስ ማመናቸው በዓለሙ ሁሉ በመሰማቱ እግዚአብሔር የማመስገኛ ምክንያቱ እንደሆነ ይገልጻል።

- ወደ ሮሜ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንደፈለገ ነገር ግን ደግሞ እንደ ተከለከለ በመግለጥ አሁን ፊት ለፊት ተገናኝቶ እንደሚያገለግላቸው ይገልፃል፡፡
    - እንዲፀኑ መንፈሳዊ ስጦታን ሊያካፍላቸው፤
    - እርስ በእርስ ለመጽናናት፤
    - በሌሎች አሕዛብ ዘንድ እንዳገኘው ፍሬ በሮሜም ለማግኘት ፤
    - የወንጌል እዳ ስላለበት በሮሜ ላሉት ደግሞ ለመስበክ መዘጋጀቱን በመግለፅ ያሳስባቸዋ፤

○ የተለየለት እና በስፍራ ሁሉ እየዞረ እንዲያደርስ የተሰጠው የምስራች መልዕክት፤ እጅግ ጠቀልል ባለመልኩ በዚህ ክፍል እንዲህ ተገልፆአል፡፡

- አስቀድሞ በነቢያት የተነገረ ተስፋ ሲሆን ይህም ተስፋ ወንጌል ነው፡፡ ይህም ወንጌል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
- እርሱም - በሥጋ ከዳዊት ዘር የተወለደ፣ በቅዱሱ መንፈስ ኃይል ከሙታን የተነሳ፤ በኃይል ከሙታን በመነሳቱ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያረጋገጠው ነው፡፡
- በዚህ ወንጌል (የምሥራች) ስብከት ሥራ አላፍርም ምክንያቱም በቅድሚያ ለአይሁድ ቀጥሎም ለአሕዛብ ሁሉ የእግዚአብሔር የማዳኑ ኃይል ነው፡፡ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር የማዳን ክብሩን የገለጠበት ደግሞም የሚገልጥበት በመሆኑ በታላቅ ደስታ እሰብከዋለሁ፡፡

## 6. ለሰዉ ሁሉ አዳኝ ማስፈለጉ 1፡17-3፡20

### *ሀ. የአሕዛብ ኃጢያተኛ መሆን 1፡17-32*

- በዚህ ክፍል ውስጥ የአሕዛብ ኃጢያተኛ መሆን የእግዚአብሔርን ቁጣ መገለጥ መሰረት በማድረግ ጳውሎስ የሚናገርበት ክፍል ነው፡፡ "ይገለጣል" የሚለው ቃል በቁጥር 17 ፣18 እና ከ19-21 ላይ ተጠቅሶአል ሁለቱ የእግዚአብሔር መገለጥ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም መሰረታዊ ሐሳብ ግን ይለያያል፡፡ የመጀመሪያው ሐሳብ የእግዚአብሔር ጽድቅ የወንጌሉን እውነት በእምነት ለሚቀበል ሰው ሁሉ ይገለጣል የሚል ሲሆን ፤ ሁለተኛው ሐሳብ ደግሞ

የእግዚአብሔርን እውነት በአመጻ ለሚገለብጡ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጥባቸዋል የሚል ነው። ሦስተኛው ግን እውነተኛ አማላክ ስለ መኖሩ እግዚአብሔር ለአሕዛብ እራሱን የተገለጠበት ነው። በእርግጥ በሥነ-መለኮት እውቀት ደረጃ መለኮታዊ መገለጥ በሁለት ሊከፈል ይችላል አጠቃላይ መገለጥ እና ልዩ መገለጥ።

- አጠቃላይ መገለጥ የሚባለው እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ በሁሉ ስፍራ ሁል ጊዜ እራሱን የገለጠበትን መንገድ ነው። ለምሳሌ በፈጠረው ፍጥረት ፣ በሕሊና ሕግ እና በታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር እራሱን ይገልጣል።
- ልዩ መገለጥ የሚባለው ደግሞ እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሰዎች በተወሰነ ስፍራ በተወሰነ ጊዜ እራሱን የሚገልጠበት መንገድ ነው። ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ እና በመንፈስ ቅዱስ እራሱን ይገልጣል።
- በዚህ ክፍል ውስጥ ግን ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ትልቅ ትኩረት የተሰጠበት በመሆኑ አራት መሰረታዊ ነገሮችን ማየት እንችላለን።
    1. የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጥ - እውነትን እያወቁ በአመፃ በሚኖሩ እና እውነትን በሚከለክሉ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ ከሰማይ ይገለጥባቸዋል።
    2. የእግዚአብሔር ቁጣ ተፈጥሮ - የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢያተኞች ንስሐ አለመግባት እግዚአብሔር የሚበይነው የመጨረሻ ፍትሐዊ በትር ነው። እግዚአብሔር በባህርይው ቅዱስ ጻድቅ እና እውነተኛ ነው፤ በመሆኑም ለሰዎች ልጆች ልቡ የሚራራ ቢሆንም በኃጢያታቸው ጸንተው የሚኖሩትን በምሕረቱም የማይደገፉትን በመቅጣት ጻድቅ እና ቅዱስ መሆኑ ይረጋገጣል። በዚህ ክፍል ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ግን ወደፊት በኃጢያተኞች ላይ የሚሆነውን ፍርድ የሚያመላክት ይመስላል። ይሁን እንጂ ከምንባቡ አውድ ደግሞ ለመረዳት የሚቻለው እግዚአብሔር በኃጢያተኞች ኃጢያት ላይ የሚሰጠው ፍርድም ሊሆን ይችላል።
    3. የእግዚአብሔር ቁጣ ምክንያት - በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ሰው በስሜት መገንፈል የሚመጣ የንዴት ማብረጃ አይደለም። ነገር ግን የሰዎች ኃጢያት ጽዋው በፊቱ እስኪሞላ ደረስ የሚታገስና ደንግጠው ከክፉ መንገዳቸው ለሚመለሱ ከቁጣው ፍርድ የሚመለስ አምላክ ነው። በዚህ የምንባብ ክፍል ግን ጳውሎስ በአሕዛብ ላይ ስለሚገለጠው የእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ ምክንያቶች ሲገልጽ

- ○ የተገለጠላቸውን የእግዚአብሔርን እውነት በአመፃኝነት በመከላከላቸው። 1፡18
- ○ እግዚአብሔርን እያወቁ ባወቁት መጠን ለእርሱ ባለመገዛታቸው። እግዚአብሔር ሕግ ለሌላቸው አሕዛብ እርሱን ያውቁት ዘንድ "የዘላለም ኃይሉን ደግሞም አምላክነቱን" በሚታዩት ነገሮች ግልጽ አድርጎ አሳይቶ ሳለ እያዩ እንዳሉ በማስመላቸው። 1፡21
- ○ እግዚአብሔርን እያወቁ ባወቁት መጠን ከማክብር ከማመስገን ይልቅ አምላክ ላልሆኑ ለተፈጥሮአዊ ነገሮች መስገድ እና ማምለከቻው ነው። 1፡23

4. የእግዚአብሔር ቁጣ ውጤት ፡- የእግዚአብሔርን እውነት እንዲሁም ስለ እውነተኛው አምላክ እውነተኛነት የተገለጠላቸውን እውነት በሐሰት ስለ ለወጡ ላደረጉት የአምጽ መንገዳቸው ተመጣጣኝ ፍርድ አግኝተዋል
   - ለሥጋቸው ወርደት እና ለልባቸው ፍትወት ለርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው፤
   - ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤
   - የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤

## *ለ. የአይሁድ ኃጢያተኛ መሆን 2፡1-3፡8*

- የእግዚአብሔር ቁጣ የሚገለጠው ሕግ በሌላቸው አሕዛብ ላይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕግ ባለቤት በሆኑት በአይሁድ ላይም እንደ ሆነ ጳውሎስ የሚያስረዳበት ክፍል ነው።
  - ○ 1-16 - አስቀድመው በሰዎች ላይ የሚፈርዱ ነገር ግን ደግሞ እነርሱም ያንኑ መልሰው የሚያደርጉ ከሚገለጠው ከእግዚአብሔር ፍርድ አያመልጡም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው በስተመጨረሻው ስለሚያስረክበው። ይህም ፍርድ አስቀድሞ በአይሁድ ላይ በኋላም በሕዛብ ላይ ይሆናል። በበደሉ እና በኃጢያቱ ንስሐ የማይገባ ሁሉ በተስመጨረሻ ላይ የሚከፈል የቁጣ ፍርድ በራሱ ላይ ያከማቻል። በመሆኑም እግዚአብሔር ሕግ ያልሰጣቸውን አሕዛብ በሕሊናቸው (በልቦናቸው) ላይ በተጻፈው ሕግ ይዳኛቸዋል።
  - ○ 1:17-3:8 - በሕግን ማውቅ እና ለሌሎች ማስተማር ከእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ አያድንም። ማወቅ እና መገረዝ ብቻ በራሳቸው ትርጉም የላቸውም ከአመጻ ጋር የሚታባበር ሁሉ የኃጢያቱን ብድራት የሚሆን ቅጣት ይቀበላል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት የአይሁዳዊ መሆኑ ምንም ብልጫ እና ማዕረግ አያሰጠውም።

ስለ እግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ የተገለጡ እንደ መመሪያ ሊታዩ የሚችሉ ሐሳቦች

1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይቻልም 2፡3
2. የእግዚአብሔር ፍርድ አለማቀፋዊ ነው 2፡9-10
3. የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ ነው ፤ እንደ ሰው ፍርድ አይዛባም 2፡2
4. የእግዚአብሔር ፍርድ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ነው 2፡6
5. የእግዚአብሔር ፍርድ አድልዎ የለውም 2፡11
6. የእግዚአብሔር ፍርድ መነሻ ሰው ሁሉ በተሰጠው ብርሃን መሰረት ነው 2፡12
7. የእግዚአብሔር ፍርድ በዘመን መጨረሻ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚፈጸም ነው 2፡16

## *ሐ. የሰው ሁሉ ኃጢያተኛ መሆን 3፡9-20*

- ከምዕራፍ 1፡17-3፡8 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ የተመለከትነው መሪ ሐሳብ በሁለት የተከፈለው የዓለም ሕዝብ በየመደቡ በሠራው ኃጢያት እና በደል ምክንያት ከእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ እንደማያመልጡ ነበር። የዚህ መሠረታዊ ምክንያት ደግሞ ሕግም የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርይያቸው በእውነት ላይ ስለማጹ ሲሆን ሕግም ያላቸው አይሁድ በሕግ መኖር ባለመቻላቸው ነው። በዚህ ክፍል ግን ሁሉም የዓለም ሕዝብ በአንድ የውድቀት ቅርጫት ውስጥ አድርጎ ሁሉም ኃጢያተኛ መሆናቸውን የሚያጸና ክፍል ነው። የሐሳቡም ማጠቃለያ ክፍል ይመስላል።
- በተለይም "አንድስ እንኳ" "የለም" የሚሉት ቃል በተደጋጋሚ የተገለጡበት እና ሰዎች ሁሉ ከኃጢያት በታች እንደወደቁ የሚያሳይ ክፍል ነው።

*"ጻድቅ <u>የለም</u> <u>አንድ ስንኳ</u>፤ አስተዋይም <u>የለም</u>፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ <u>የለም</u>፤ **ሁሉ ተሳስተዋል**፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ <u>የለም</u>፥ <u>አንድ ስንኳ</u> <u>የለም</u>።" 3፡ 11-12*

## 7. እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያዘጋጀው አዳኝ 3፡21-5፡21

### ✧ *የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ማብራሪያ 3፡21-31*

- ሁሉም ኃጢያትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል በመሆኑም በሕግ እና በነቢያት መጻሕፍት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል።ይህም የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ ደም የሕይወት ምትክነት የተገኘ በመሆኑ እግዚአብሔርም ጻድቅ መሆኑን አሳይቶአል።
- እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ ሳይሆን የአሕዛብም አምላክ በመሆኑ ሁሉም በእምነት የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ተካፋይ ሆነዋል።

### ✧ *የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ተምሳሌዎች 4፡1-25*

- ጳውሎስ ለሰው ልጆች ሁሉ መዳን ይሆን ዘንድ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ጽድቅ በሕግ ሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ የሚገኝ መሆኑን በአብርሃም እና በዳዊት ምሳሌነት ሊያስረዳ የሚሞክርበት ክፍል ነው።
    - አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት እምነቱ እንጂ ሥራ አልነበረም፤ በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ የሚመካበት ነገር ይኖረው ነበር። ደግሞም ጽድቅ በሥራ ከሆነ ደሞዝ እንጂ ጸጋ ሊሆን አይችልም፤ 4፡1-6
    - አብርሃም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያገኘው ከመገረዙ በፊት እንጂ ከተገረዘ በኋላ አይደለም። በመሆኑም የአብርሃም ግረዘት በእምነቱ ለተቀበለው የእግዚአብሔር ጽድቅ ማህተም እንዲሆነው ነው። በተጨማሪም ሳይገረዙ ጽድቅን ለሚቀበሉ ሁሉ በእምነታቸው አባት እንዲሆን ነው። 4፡9-12
    - አብርሃም ከእግዚአብሔር የተነገረውን የተስፋ ቃል ያገኘው/የተቀበለው በእምነቱ እንጂ በሕግ ወይም በሥራ አልነበረም። "ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ" ተብሎ የተነገረውን የተስፋ ቃል በብዙ እምነት አገኘ ወረሰውም። 4፤13-25
    - ዳዊትም በመዝሙሩ ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ሰው ተናግሮአል። ኃጢያታቸው ስለተከደነላቸው ስለ ተሰረየላቸው ሰዎች እድለኛነት ሲናገር ምስጉኖች ናቸው ወይም ብጹዓን ናቸው ብሎአል። 4፡6-8

### ✧ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ትሩፋቶች 5፡1-11

- በክርስቶስ ሥራ የተገለጠው እና በእምነት የምንቀበለው የእግዚአብሔር ጽድቅ ብዙ መንፈሳዊ በረከቶችን ይዞ መጥቶአል። ከእነዚህም መካከል በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ብቻ መመልከት መልካም ነው ለጥናታችን።
  - ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን፤
  - በእምነት ወደ እግዚአብሔር ጸጋ መግባትን አግኝተናል፤
  - በሚደርስብን መከራ ሁሉ ፍጹም ደስተኛ መሆን፤
  - ዘላለማዊ አምላክ መለኮታዊ ፍቅሩን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን ውስጥ አፍስሶታ፤
  - ገና ደካሞች ሳለን ዘመኑ ሲደርስ ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን፤

### ✧ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ መሰረቱ 5፡12-21

- በዚህ ክፍል ውስጥ እጅግ በሚገርም መንገድ በመጀመሪያው አዳም እና በክርስቶስ በኩል ስለመጣው ጥልቅ የሆነ ያለመታዘዝ መንገድ እና የጽድቅ መንገድ አውራ መሰረቶች እንደሆኑ ይገልጻል
- በአንዱ አዳም አለመታዘዝ  ፡- ኃጢያት ወደ ዓለም ገባ፤

  - ሞት በሰው ሁሉ ላይ ነገሠ፤

  - ፍርድ ለኩነኔ ለሰው ሁሉ ደረሰ፤

  - ብዙዎች ኃጢያተኛ ሆኑ ፤

  ❖ በደል በዓለም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ !
- በአንዱ በኢየሱስ መታዘዝ ፡- ጸጋ ወደ ዓለም ገባ ለብዙዎችም በዛ፤

  - ሕይወት በሚያምን ሁሉ ላይ ነገሠ ፤

  - ብዙዎችም ጻድቃን ይሆናሉ፤

## 8. በወንጌል የመጣ የነጻነት መንገድ 6-7

### ✧ ከኃጢያት ባርነት ወደ አርነት 6፡1-23

- በሕግ የሚገኝ ጽድቅ የለም ሲባል ዘወትር የሰውን ልብ የሚይዘው ጉዳይ ኃጢያትን ለማድረግ ነጻ ነኝን የሚለው ጥያቄ ነው። በመሆኑም ሐዋርያው ሐሳቡን የሚጀምረው በክርስቶስ ወንጌል የእግዚአብሔርን ጽድቅ በእምነት የተቀበሉ ሁሉ ከዚህ በኋላ በኃጢያት ጸንተው አይኖሩም ምክንያቱም
- ባመንን ጊዜ ተጠምቀናል በመሆኑም
  - ከክርስቶስ ጋር ሞቱን በሚመስል ሞት ሞተናል ፤
  - ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እኛም በአዲስ ሕይወት ለመላለስ ከሞትንበት ተነስተናል፤
  - አሮጌው ሰውነታችን/ የኃጢያት ተፈጥሮ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎአል፤
- ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ እንደገና ላይሞት ነገር ግን ለዘላለም በሕይወት እንደሚኖር እኛም እንደዚሁ አንድ ጊዜ መሞትን ለኃጢያት በመሞት ለአዲስ ሕይወት ስለተነሳን ይህንን በእምነት መቀበል እና መቁጠር ነው። በመሆኑም ሰውነታችን የጽድቅ ባሪያዎች ብቻ አድርጎ ማቅረብ ነው ያለብን።

### ✧ ከሕግ ባርነት ወደ አርነት 7፡1

- በተለይ ሥለ ሕግ እውቀት እና መረዳታ አለን ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ሐዋርያው ሕግ ሊሰራ የሚችለው ሰውዬው ካልሞተ ብቻ ነው የሚል ምሳሌያዊ ገለጻ ያደርጋል። ይህንን ሐሳብ ለማስረዳት የጋብቻ ቃል ኪዳን ምሳሌ በማሳየት አማኝ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድሎአል በመሆኑም በመጪው ዘመኑ ለሞተለት ለክርስቶስ ይኖራል እንጂ ለራሱ አይኖሩም። በቀጣይም በአዲሱ በመንፈስ ቅዱስ ባለ የሕይወት ሥርዓት ይመላለሳል እንጂ በአሮጌው በፊደል ሥርዓት አይኖርም። 7፡1-6
- የሕግ መምጣት በሰዎች ላይ ያስከተለውን ሌላ ጉዳይ ጳውሎስ በቀጣይነት ያነሳል ይኸውም ሕግ ከመምጣቱ በፊት ሰዉ ሕያው ነበር ነገር ግን ሕግ ከመጣ በኋላ ኃጢያት ጉልበት አግኝቶ ሞትን ወለደ። ስዚህም ለሕይወት የተሰጠው ትዕዛዝ/ሕግ ኃጢያትን ምክንያት አድርጎ ገዳይ ሆነ። 7፡7-11

- ታዲያ ሕግ ምንድር ነው ክፉ ነው ማለት ነው? አይደለም ! ሕጉ በራሱ ቅዱስ ፣ ጻድቅ ፣ በጎ እና መንፈሳዊ ነው። ነገር ግን ኃጢያት በሕጉ ምክንያት ጉልበት አግኝቶ ሞትን አስከተለ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ተሸናፊ የሆነው የእኔ የውስጥ ማንነት ነው። 7፡12-14
- ከቁጥር 15-25 ያለው ክፍል እጅግ አወዛጋቢ የሆነ የምንባብ ክፍል ቢሆንም ቅሉ በተቃራኒው ደግሞ እጅግ በጣም የሚገርም እውነትን የሚያስረዳ ነው። በተለይም ደግሞ የእግዚአብሔር ሕግ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የሚሟገተን ሕግ ከውስጣችን ሆኖ የምንመኘውን፣ የምናስበውን እና በጎ የሆነው ነገር ማድረግ ያለመቻላችን ታላቅ ሚስጥር የተገለጠበት ክፍል ነው። ከዚህ የተነሳ ታላቅ የሆነ የእርዳታ ጩኸት የሚሰማበት ክፍል ነው ፤ "እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" ከዚህ ትግል ለመዳን የቀረበ የውስጥ ጩኸት ነው።

## 9. በመንፈስ ቅዱስ የተገኘ አርነት 8

✧ *በመንፈስ ቅዱስ የተመራ ሕይወት 8፡1-17*

- በመንፈስ ቅዱስ የሆነው አዲሱ የመንፈሳዊ ሕይወት ሥርዓት ከኃጢያት እና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶናል። በመሆኑም እንደ አዲሱ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚመላለሱ ሁሉ የመንፈስን ነገር ያስባሉ ስለ መንፈስ ማሰብ ደግሞ ሰላም ነው። እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚመላለሱ ሁሉ ግን የስጋን ነገር ያስባሉ እግዚአብሔርንም ደስ ማሰኘት አይችሉም።
- በመሆኑም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውንም በውስጣቸው የሚኖረው መንፈስ ይመሰክራል ይህም መንፈስ አባ አባ ብለው የሚጮኹበትን የልጅነት ክብር አጎናጽፎአቸዋል።

✧ *የወደፊቱ የአማኝ ክብር 8፡18-27*

- የእግዚአብሔር የልጅነት ክብር የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ወራሽ የመሆን መብትን አጎናጽፎናል። ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ከሆንን ከእርሱ ጋር ደግሞ አብረን መከራውንም እንቀበላለን። ይሁን እንጂ ለእኛ እግዚአብሔር ካዘጋጀው እና ሊገለጥም ካለው የልጅነት የወራሽነት ክብር ጋር ሲመዛዘን የአሁኑ ዘመን መከራ ወይም ስቃይ ምንም ማለት አይደለም።

- በእርግጥ ይህንን የእግዚአብሔር ልጆች ክብር መገለጥ በተስፋ ይምንጠብቀው ጉዳይ ነው እንዲሁም መዳናችም ጭምር በተስፋ ነው። እኛም ብቻ ሳንሆን ፍጥረት በሙሉ በታላቅ ናፍቆት የሚጠባበቀው እለት የእግዚአብሔር ልጆች የክብር ነጻነት ቀንን ነው።

*✧ ከአሸናፊዎች በላይ የሆነ አሸናፊነት 8:28-39*

- በእርግጥ ይህ ክፍል በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠው የእግዚአብሔርን ጽኑ ፍቅር ማንም ምንም ሊያግተው እና ሊያጠፋው የማይቻል መሆኑን የሚገልጥ ነው። የሚሆነው ነገር ቢሆንም እንኳን ለበጎ ነው የሚደረገው እንጂ ከእግዚአብሔር ሊነጥለን የሚችል አይደለም። ምክንያቱም እርሱ አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፣ የጠራቸውን አጸደቃቸው ፣ ያጸደቃቸውን ደግሞ አከበራቸው እንዲህ ካለው ፍቅር ሊነጥል የሚችል ምንም ነገር የለም። በተጨማሪም በክርስቶስ አሸናፊ ከሚመስሉ ሁሉ በላይ አሸናፊዎች በመደረጋችን ነው። በእርግጥ የእግዚአብሔር ፍቅር የገዛ ልጁን ምንም ሳይራራ አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ነው። እንዲሁም ሌላውንም ነገር እንዲያው ለመስጠት የታመነ ነው።
- የእግዚአብሔርን ፍቅር ታላቅነት ለማሳየት የቀረቡ ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
    1. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ <u>ማን ይቃወመናል</u>? 8:31
    2. ….ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው <u>እንዴት አይሰጠንም</u>? 8:32
    3. እግዚአብሔር የመረጣቸውን <u>ማን ይከሳቸዋል</u>? 8:33
    4. የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ <u>የሚኰንንስ ማን ነው</u>? 8:33
    5. ከክርስቶስ ፍቅር <u>ማን ይለየናል</u>? 8:35

## 10. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አጀንዳ ለእስራኤላዊያን 9-11

- ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ ዘመዶቹ ስለ ሆኑት ስለእስራኤላዊያን የሚሰማውን የግል ቁጭት እና ቅናት በሰፊው የገለጠበት ክፍል ነው። ብዙ ኀዘን ፣ የማያቋርጥ ጭንቀት ፣ ከክርስቶስ ተለይቶ የተረገመ እንዲሆን እስኪመኝ ደረስ ጸልዮአል በአገልግሎቱም ቢሆን በአሕዛብ ዘንድ በሚሰብከው ወንጌል አይሁድን አስቀንቶ ወደ መዳን ለመመለስ በብዙ ጥሮአል። በዚህ በሮሜ መልዕክቱ ግን አጠቃላይ ዘለዓለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን አጀንዳ ከእስራኤላዊያን መዳን አንጻር ግልጽ ሐሳቡን ሲያስቀምጥ ምናልባትም ከአሕዛብ ወገን ካመኑት መካከል እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አሕዛብ

መመለሱን በማየት የትዕቢትን ነገር የሚያስቡ ያሉ ይመስላል እነርሱን ለማስተማር ሳይሆን አይቀርም። 11፡17-22

### ✧ የእስራኤል መመረጥ 9፡1-29

- አይሁዳዊያን በእርግጥ የእግዚአብሔር ትልቅ ዓላማ ያረፈባቸው ሕዝቦች ናቸው። በመሆኑም በሁሉም አቅጣጫ ከአሕዛብ ብልጫ አላቸው የተሰጣቸውን በረከት እድል መመልከቱ ብቻ በቂ ነው። የእግዚአብሔር ባርኮት በሕዝበ እስራኤል መካከል፡-
    1. እስራኤላዊያን ናቸው ፤
    2. ልጅነት (adoption) የተሰጣቸው ፤
    3. የእግዚአብሔር የመገኘቱ ክብር (Shekinah) የተቸራቸው ፤
    4. የቀደመውን ኪዳን ተቀባዮችና በለቤቶች፤
    5. የሕጉ ተቀባዮች፤
    6. የመቅደስ ሥርዓት ተቀባዮች፤
    7. የተስፋውን ቃል ተቀባዮች፤
    8. የእምነት አባቶቹ ከእነርሱ የሆኑ እና
    9. የሰዎች ልጆች መዳን ቤዛ የሆነው ክርስቶስ ከእነርሱ የመጣ ሕዝቦች ናቸው።
- የእስራኤላዊያንን ምርጫ በተመለከተ እንደ ተስፋው ቃል የተወለዱ ብቻ እንጂ ከአብርሃም የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለም እንዲሁም ከይስሐቅ። ይህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም ከአሕዛብም መካከል እንደ ተስፋ ቃል የተወለዱት ሁሉ እስራኤላዊያን ናቸው የተመረጡም ናቸው።

### ✧ የእስራኤል አለማመን 9፡30-10

- ከላይ የተዘረዘሩት አስገራሚ እድሎች ያሉአቸው እነዚህ ሕዝብች በሕግ እና በነቢያት የተመሰከረለትን በእምነት የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ግን ማግኘት አልቻሉም። ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው፡-
    - በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ፤
    - በጺዮን በተቀመጠው የመሰናከያ ድንጋይ ስለ ተሰናከሉ፤

- ቅናታቸው በእውቀት ላይ የተመሰረት ባለመሆኑ፤
- የእግዚአብሔርን ጽድቅ ትተው በራሳቸው ለራሳቸው ጽድቅ ማቆም ስለፈለጉ፤
- በተሰበከላቸው የምሥራች ወንጌል ባለማመናቸው ምክንያት ነው።

### ✧ *የእስራኤል የተሐድሶ ጊዜ 11*

- የክርስቶስን ወንጌል አምነው እና ተቀበለው መዳን የሚጠበቅባቸው እስራኤላዊያን ይህንን ባለማድረጋቸው እግዚአብሔር እስከ ለዘላለሙ ጣላቸው ማለት ነው? ፈጽሞ አይደለም እግዚአብሔር አልጣላቸውም በጸጋ የዳኑ ቅሬታዎች አሉ። ለኤልያስ የተመለሰለት መለኮታዊ መልስ እንደ መረጃ ቀርቦአል።
- በጸጋ ባልዳኑት እስራኤላዊያን የሕዝብ ሙላት እስኪደርስ ድረስ የእንቅልፍ እና የድንዛዜ መንፈስ ወድቆባቸዋል።
- አሕዛብ አስቀድሞ አልታዘዙም ነበር ከዚህም የተነሳ ምሕረትን አግኝተዋል። በቀጣይ ደግሞ እስራኤላዊያንም ባለመታዘዛቸው ምክንያት ምህረትን ይቀበላሉ። በመሆኑም እስራኤል ሁሉ ይድናሉ። እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ አይሁድንም ሆነ አሕዛብን ሰውን ሁሉ ካለመታዘዝ በታች ዘግቶታል።
- የምዕራፍ 9 ፣10 እና 11 የማጠቃለያ ሐሳብ ገላጭ ሊሆን የሚችለው ይህ ጥቅስ ነው እስቲ ልብ ብለን እንመልከተው ፤

*የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።*

*የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው?*

*ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?*

*ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።*

*ሮሜ 11፡33-36*

## 11. በእውነተኛው የወንጌል ሥርዓት መመላለስ 12፡1-15፡7

### ✧ ክርስቲያናው የኑሮ እና የአገልግሎት ሥርዓት 12፡1-21

- ዕለታዊ የክርስቲያን ኑሮ እና አገልግሎት ምን መሆን እንዳለበት ለሮሜ አማኞች የገለጻቸው ሐሳቦች ዛሬም ላለነው አማኞች አጅግ ወሳኝ ተግባሮች ናቸው፡፡
- ከእነዚህም መሐል
    - ሰውነትን ለእግዚአብሔር ሕያው ቅዱስ እና ደስ የሚያሰኝ አደርጎ ማቀረግ መቻል፤
    - የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈትኖ ለመረዳት በአዕምሮ ለመለወጥ መታደስ ማቻል፤
    - በተለያየ ጸጋ ስጦታ የሚያገለግሉ ሰዎች የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ በተሰጣቸው ጸጋ ለማገልገል ይችሉ ዘንዳ ራሳቸውን እንደ አንድ የአካል ብልት አድርገው እንዲቆጥሩ፤ አካሉም ክርስቶስ እንደ ሆነ ማሰብ እንዲችሉ፤
    - እርስ በእርስ በወንድማማች ፍቅር መዋደድ መቻል፤

### ✧ ከመንግስት ባለሥልጣን እና ከሰዎች ጋር ሊኖር የሚችል ክርሰቲያናዊ የኑሮ ሥርዓት 13፡1-14

- የመንግስት ባለ ሥልጣናት የሹመታቸው ምንጭ እግዚአብሔር በመሆኑ በአግባቡ መገዛት መቻል የመልካም ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር አካል ነው፤የመንግስት ባለ ሥልጣናት ለመልካም ነገር የሕዝብ አገልጋዮች ናቸው ለአመጸኞች እና ሕግ ሌላቸው ደግሞ ቁጣውን ለመበቀል የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለመንግስት ግብር መገበር ደግሞም ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት ተገቢ መሆኑን ጳውሎስ በምክሩ አሳይቶአል፡፡
- ከሰዎች ሁሉ ጋር ሊኖር ስለሚቻል ዕለታዊ ኑሮን በተመለከተ የሕግ ሁሉ ፍጻሜ የሆነውን ፍቅርን መኖር ከሁሉ ሰው ጋር ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡
- ከመቼውም ጊዜ ይልቅ መዳናችን ወደ እኛ ስለቀረበ የብርሃንን ጋሻ ጦር ወይም ክርስቶስን መልበስ እንጂ በስካር፣በዘፈን፣በመዳራት፣በዝሙር፣ በክርክር እና በቅናት መመላለስ ግን በደጅ ያስቀራል፡፡

### ✧ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራ እና ደካማ በሆኑ ሰዎች መካከል ሊኖር የሚችል ክርስቲያናዊ የኑሮ ሥርዓት 14፡1-15፡7

- ይህ ረጅም ክፍል የትምህርቱ መሰረተዊ ሐሳብ በሮም አማኞች መካከል ያል የውስጥ ችግር ይመስላል። ምክንያቱም ሐዋርያው የሚያነሳቸው ሐሳቦች በደካሞች እና ጠንካራ የመንፈሳዊ ሕይወት ባላቸው መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥፋት የሚችል ትምህርት በመሆኑ ነው።
- ቀንን በሚያከብሩ እና ሥጋን በሚበሉ ወንድሞች ላይ የፍርድ ቃልን የሚያወጡ እና በመካከላቸውም መናናቅ ያለ ይመስላል። በመሆኑም ይህ ጉዳይ
    - በክርስቶስ ፍቅር አለመመላለስ ነው፤
    - በክርስቶስ እምነት ያለ ማንም ቢሆን ለራሱ የሚኖር የለም በመሆኑም ለሌሎች መኖር አለመቻል ነው፤
    - የእግዚአብሔር መንግስት የደስታ የሰላም እና የጽድቅ መንግስት ናት እንጂ የሙብል እና የመጠጥ ጉዳይ ያለባት አይደለችም በመሆኑም የእግዚአብሔር መንግስት አጀንዳ በልሆነ አጀንዳ ላይ እራስን አሳልፎ መስጠት ነው፤
    - ብርቱዎች የደካሞችን ሸክም መሸከም አለመቻል ነው፤
    - ክርስቶስ እራሱን አላስደሰተም እኛም እያንዳንዳችን ራሳችንን የምናስደሰት ለወንድማችን ደስታ ስፍራ ከሌለን የክርስቶስን ምሳሊያዊ ኑሮ መከተል አለመቻል ነው፤
    - ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር በፍቅር ገና በኃጢያት በጨላማ ሳለን እንደተቀበልን ሌሎችን እንዲሁ በክርስቶስ በጋለ ፍቅር መቀበል አለመቻል ነው፤ በመሆኑም ወደ ትክክለኛው የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ ውስጥ መደረግ ያለበትን ነገር በማሳሳብ ለዛሬውም የክርስትና ኑሮ መሰረት የሚሆን እውነት የተገለጠበት ክፍል ነው።

## 12. ሰላምታ እና የማጠቃለያ ሐሳብ 15፡8-16፡27

✧ *የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት በአሕዛብ መካከል 15፡8-33*

- እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአሕዛብም በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነው በረከት ሁሉ እንደ ሚበዛላቸው ተስፋ በሰጠው መሰረት በሮሜ የሚገኙትም ከዚህ የበረከት ተስፋ ደስታን እና ሰላምን እንዲሞሉ ይባርካቸዋል። በእርግጥም የሮሜ አማኞች የበሰሉ መሆናቸው በብዙ የእግዚአብሔር በረከት እንደ

ተሞሉ ጳውሎስ ቢረዳም በተሰጠው የክርስቶስ ወንጌል ኃላፊነት በድፈረት ይህንን መልዕክት ጽፎላቸዋል፡፡

- ትልቅ ድፍረት እና ትምክት የሆነው በአሕዛብ መካከል በሚሰብከው ወንጌል ጌታ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእርሱ የሚሠራው ሥራ ነው፡፡ በአገልግሎቱም አስቀድሞ የክርስቶስ ስም ባልተጠራበት ስፍራ ነበር፡፡ በመሆኑም ከኢየሩሳም ጀምሮ እስከ እልዋሪቆን ድረስ ወንጌል ሰብኮአል፡፡
- ወደ ሮሜ ለመምጣት እና በሌሎች ስፍራ እንዳገነው አይነት የወንጌል ፍሬ ለማግኘት በብዙ ናፍቆት ቢፈልግም እንዳይመጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳልተፈቀደለት ነገር ግን ወደ እስጳንያ ሲያልፍ እንደሚጎበኛቸው አሁን እርዳት ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ሚሔድ ያስታውቃቸዋል፡፡
- በወንጌል አገልግሎቱም በጸሎታቸው እንዲደግፉት ይጠይቃቸዋል፤
    - አብረውት እንዲጋደሉ ፤
    - በይሁዳ ካሉት ሰዎች ጌታ እንዲያተርፈው፤
    - በኢየሩሳሌም ያለው አገልግሎቱ ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን፤

✧ *የጳውሎስ ሰላምታ ለወዳጆቹ 16፡1-16*

- በተለያየ ሁኔታ ለሚያውቃቸው እና በአገልግሎቱ አጋር ሆነው አብረው ለደከሙት ሁሉ በስም እየጠራ ሰላምታ አቅርቡልኝ በማለት ጽፎአል፡፡

✧ *የጳውሎስ የደብዳቤው/የመልዕክቱ ማጠቃላያ ሐሳብ 16፡17-27*

- ምክር ባርኮት እና የተረፉ ሰላምታዎች የተካተቱበት ክፍል ነው፡፡

## ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን

## አሜን !